# ክፍል አምስት

## አመራርና ተጠያቂነት

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ባለ አደራነትና ተጠያቂነት ያለው አመራር

- *"ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከንፈሮቹ እውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፤ ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል::" (ሚልክያስ 2÷ 7)*
- *"እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቁጠረን:: እንደዚህም ሲሆን በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል::" (1ቆሮ. 2÷ 1-2)*
- *"የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎች አይደለንምና፤ በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር እንደ ተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን::" (2ቆሮ. 2÷ 17)*
- *"አገልግሎታችንም እንዳይነቀፍ በአንዳች ነገር ማሰናከያ ከቶ አንሰጥም:: ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤" (2ቆሮ. 6÷ 3-4)*
- *"የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና:: ... ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ::" (ፊል. 4÷ 11÷ 13)*
- *"ነገር ግን ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን÷ እንዲሁ እንናገራለን፤ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ÷ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም::" (1ተሰ. 2÷ 4)*
- *"መልካሙን አደራ በእኛ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ጠብቅ::" (2ጢሞ. 1÷ 14)*
- *"የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ::" (2ጢሞ. 2÷ 15)*

## I. መግቢያ፡-

የቤተ ክርስቲያን አመራር በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ሕዝብ ፊት በታማኝነት ለማገልገል ካስፈለገ ባለ አደራነት (STEWARDSHIP) እና ተጠያቂነት (ACCOUNTABILITY) ያለው ሕይወትና አገልግሎት ሊኖረን ይገባል ብዬ አምናለሁ:: ባለ አደራ መሆናችንን ካላስተዋልን እግዚአብሔር የሰጠንን የጸጋ ስጦታዎች፥ ጊዜና፥ ገንዘብ (ንብረት) እርሱን በማክበር ከምንይዘውና በአግባብ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መታነፅ ከምንጠቀምበት ይልቅ፤ ለግል ጥቅም፥ ለራስ ክብርና፥ የውስጣችን ሥጋዊ ፍላጎት መሟያ ልናደርገው እንችላለን:: በተጨማሪም ተጠያቂነት ያለው ሕይወትና አገልግሎት ካልኖረን እንድናገለግለው የተጠራንለትን ሕዝብ ከማክበር ይልቅ፥ ለመናቅ፤ ከምናሳድገው ይልቅ፥ ለማቀጨጭ፤ በእግሩ እንዲቆም በጌታ ቃል ከማጎልበት ይልቅ፥ ተደጋፊ እንዲሆን ለማድረግ እንፈተናለን:: የተሰጠን የጸጋ ስጦታም ለሕዝቡ ሲባል እንደ ተሰጠን አውቀን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ከመያዝ ይልቅ፥ በሕዝቡ ላይ መሰልጠን እንጀምራለን:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አመራር ጤነኛና ዘላቂነት ያለው እንዲሆን ካስፈለገ ባለ አደራነትና ተጠያቂነት ምን እንደሆነና ለአመራራችንም ያለው አንድምታ ልንዳስስ ይገባል ብዬ አምናለሁ::

## II. ትርጉመ ወሰን፡-

### ሀ. ባለ አደራነት፡-

<u>ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት ከእግዚአብሔር የተሰጠን የፀጋ ስጦታዎች፥ የጥበብና የእውቀት ባለጠግነት፥ ጊዜና ዘመን፥ ገንዘብና ንብረት በጌታ ፍርሃት በመ ገዛት ለእግዚአብሔር ክብርና ለሕዝቡ ጥቅም ማዋል ነው:: ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት የሕይወታችንና የአገልግሎታችን መሠረት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል በማስተዋልና በጥንቃቄ በግላችን ማንበብ፥ መስማትና መታዘዝ፤ ከዚያም በትጋትና በመሰጠት መስበክ፥ ማስተማር፥፥ ማወጅ፤ እንዳይበረዝ፥ እንዳይቀየጥ፥ እንዳይሸራረፍና፥ እንዳይመቻመችም መጠበቅ፤ ከእኛም በኋላ ለሚመጣው ትውልድም በንጽሕናው ማስተላለፍ ነው!!!</u>

ፒተር ብሎክ የሚባል ጸሐፊ እንዲህ ይላል፥ "ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት ኢንስቲቱሽኖች የኃይል፥ የዓላማ፥ የምስጋና ሥርጭት ለመቆጣጠር የሚተዳደሩበት ደንብ ነው:: ባለ አደራነት ወይም መጋቢነት ለትልቁ የክርስቶስ አካል ደህንነት

ተጠያቂ መሆንና ለመገልገል ከመፈለግ ይልቅ፥ ማገልገልን መምረጥ ነው::"[384]

የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ይላል፥

*"ወንድሞች ሆይ፥ ስለ አንዱ በአንዱ ላይ አንዳችሁም እንዳይታበዩ ከተፃፈው አትለፍ የሚለውን በእኛ ትማሩ ዘንድ፥ ይህን በእናንተ ምክኒያት ስለ ራሴና ስለ አጵሎስ እንደ ምሳሌ ተናገርሁ:: አንተ እንድትበልጥ ማን አደርጎሃል? ያልተቀበል ኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?'* (1ቆሮ. 4፥ 6-7)

## ለ. ተጠያቂነት:-

ተጠያቂነት ማለት የምናገለግለውን ሕዝብ፥ አብረውንም የሚያገለግሉትን ሌሎች መሪዎች እንዳንጎዳ፤ ወይንም መጠቀሚያ እንዳናደርጋቸው ለማገድ የመጠበቂያ መለኪያና ሚዛን ዘዴ ነው:: ይኸን ለማድረግ የሚያስችለን እንደ መሪዎች የምናስበውም ይሁን፥ የምናደርገው ነገር ሁሉ በብርሃን፥ በግልፅነትና፥ ለምክርና ለተግሳጽ (ለእርማት) ክፍት በመሆን ነው!!! የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከጌታም ሆነ ከምናገለግለው ሕዝብ የሚጠበቅብን ተጠያቂዎች፥ እና ምላሽ መስጠት የሚገባን ሰዎች መሆናችን ነው:: ተጠያቂነት ከሌሎች አገልጋዮችም ይሁን፥ ከበሰሉና ቀልፍ ከሆኑ ምዕመናን ጋር ስለ ሕይወታችንና ስለ አገልግሎታችን ግልፅነትና እውነተኛነ ት ባለው ሁኔታ ለመነጋገርና ለመወያየት ያስችለናል::

*"አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደልምና:: ... ዓይን እጅን አታስ ፈልገኝም ልትለው አትችልም፤ ወይም ራስ ደግሞ እግሮችን አታስፈልጉኝም ሊላቸ ው አይችልም:: ... አንድም ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሠቃያሉ፤ አንዱ ብልትም ቢከብር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል::'* (1ቆሮ. 12፥ 20-21፥ 26)

# III. የባለ አደራነትና ተጠያቂነት ሥነ መለኮታዊ መሠረት:-

## ሀ. የአመራር ዘይቤዎች (METAPHORS):-

(1ተሰሎንቄ 2፥ 1-13)

1. የባለ አደራ ወይም መጋቢ ታማኝነት:-

---

[384] Peter Block, *Steard: Choosing Service Over Self-Interest,* (San Francisco, CA: Berrett-Koehler, 1993), XX.

"*ነገር ግን ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፥ እንዲሁ እንናገራለን፤ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ፥ ሰውን ደስ እንድምናሰኝ አይደለም።*" (ቁጥር 4)

2. የባለ አደራ ወይም መጋቢ እርጋታ፥ ቅንነትና፥ ፍቅር፡-

"ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንድምትንከባከብ በመካከላችሁ የዋሆች ሆነን እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፤ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና።" (ቁጥር 7)

3. የባለ አደራ ወይም መጋቢ የማበረታታት አገልግሎት፡-

"ወደ መንግሥቱ፥ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጸናን፥ እየመሰከርንላችሁም፤ አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደሆንን ታውቃላችሁና።" (ቁጥር 11-12)

4. የባለ አደራ ወይም መጋቢ የመስበክ/ የማወጅ ድፍረት፡-

"የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን።" (ቁጥር 9)

❖ *የእምነት ሰው የሆነ መሪ ታማኝ በመሆን የተመሠከረለት፤ እንደ እናት በርህራኄ፥ በፍቅርና፥ በእርጋታ የተሞላ፤ እንደ አባት ደግሞ ለማበረታታት፥ ለመምከር፥ ለመገሰፅና፥ ለመምራት የሚችል ነው። ከዚህም ሌላ እንደ አዋጅ ነጋሪም የእግዚአብሔርን ቃል በትሕትናና በድፍረት፥ በቅንነትና በማስተዋል፥ እየሰበከ ቃሉን ሳይሸቃቅጥና ሳያመቻምች የሚኖረውን የሚሰብክ፥ የሚሰብከውንም የሚኖር ሊሆን ይገባዋል*!!!

❖ እንደ እግዚአብሔር ሰዎችና እንደ ባለ አደራ የእግዚአብሔርን ቃል ለመጠበቅና ለማወጅ ኃልፊነት አለብን። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ እናትና እንደ አባት በርህራ ኄ የመውደድ፥ የመምከርና፥ የማበረታታት ኃላፊነት አለብን። ይኸን ለማድረግ የሚያስችለን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፍቅርንና እውነትን በሚዛን ጠብቀን፥ በፍቅራችን ውስጥ እውነትን፥ በእውነታችንም ውስጥ ደግሞ ፍቅርን ለመለማመድ ስንችል ነው። ምክኒያቱም እውነት የሌለው ፍቅር የማይጨበጥ፥ ብስለት የጐደለው፥ እና ይዘት የሌለው የስሜት ግልቢያ ነው። ፍቅር የሌለው እውነት በአንፃሩ በትር ሆኖ ሰውን የሚያቆስል፥ ሌላውን የሚሰብር፥ ከሚያንፅ ይልቅ የሚያፈርስ የትዕቢት መግለጫ ነው።

## ለ. ተጠያቂነትና የሰው ክቡርነት:-

### 1. የእግዚአብሔር ቃል ስለ እኛ አስረግጦ የሚናገረው:-

1.1 የእኛ አለማወቅ:- "ኢየሱስም:- አባት ሆይ÷ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው፤ አለ::" (ሉቃስ 23÷ 34)

1.2 የእኛ ድካም:- "አቤቱ እኛ አፈር እንደሆንን አስብ::" (ዕዝራ 9፤ ነህምያ 9፤ ዳንኤል 9)

1.3 ነገር ግን እግዚአብሔር ለምናስበውና ለምናደርገው ነገር ሁሉ ተጠያቂዎች እንድንሆን ሰብዓዊ ክብራችንን ጠብቆ በፊቱ በኃላፊነት ያቆመናል::

1.4 ምንም እንኳን ለሌሎች ሰዎችም ተጠያቂዎች ብንሆንም፤ በመጀመሪያ ደረጃ ግን በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂዎች ነን:: አሁን በጌታ ፊት ተጠያቂነት እንዳለው ሰው የቆምነውን ያህል፤ አንድ ቀን ጌታ ራሱ በክብር በሚመጣበትም ጊዜ ፍና በፊቱ እንቆማለን:: ወይ አክሊሉ እንደ ተወሰደበት ሰው "ነፍሳችን ብቻ በእሳት እንደሚድን ድና" (1ቆሮ. 3÷ 10-15) በፊቱ ለመቆም፤ ወይንም ደግሞ "አንተ በጎ ታማኝ ባርያ÷ በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ::: የሚለውን አስደናቂ የጌታ ድምፅ (ማቴ. 25÷ 21÷ 23) በመስማት በፊቱ በክብር እንቆማለን!!! *<u>በመሠረቱ እግዚአብሔር የጠራን ስኬታማነት ያለው ሰው እንድንሆን ሳይሆን÷ ታማኝነት ያለው የእግዚአብሔር ሰው እንድንሆን ነው!!!</u>*

1.5 ስለዚህም ነው የሰዎች አስተያየት በጣም ከፍ አድርገን በመውሰድ፤ በአንድ በኩል ደግሞ በአገልግሎታችን ትችትና ነቀፌታ ሲመጣ ልባችን ሊወድቅና ተስፋ ልንቆርጥ÷ በሌላ በኩል ባሞገሱን ጊዜ ደግሞ ልባችን ሊኮፈስና ሊኩራራ የማይገባው::

1.6 እንደ እግዚአብሔር ሰዎች ሁልጊዜ ማሰብ ያለብን "ሰው ፊትን ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል::" የሚለው ቃል ነው:: (1ሳሙ. 16÷ 7)

1.7 እግዚአብሔር ከድርጊታችን በላይ የሐሳብ ሂደታችንን÷ ውስጣዊ መንስኤ አችንን÷ መነሻ ጥንስስ ሐሳባችንን ያነባል፤ ያውቃልም:: በእርሱ ፊት ተጠያቂ መሆን ከሰዎች ትችትና ነቀፌታ÷ እና ከሰዎች ሙገሳና ሆታ በላይ እንድንኖር ያደርገናል::

**2. መለኮታዊ ጥሪና የሰው ክቡርነት፦**

2.1 በመጀመሪያ የሰውን ክቡርነት እናስረግጣለን። ምክኒያቱም የሰው ልጆች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን፥ እርስ በርሳችንም ለማገልገል እንደ ተጠራንና የክርስቶስን አካልና የእግዚአብሔርንም ፍጥረት በባለ አደራነት/ በመጋቢነት ለመምራት የተጠራን ነን። ስለዚህም ሰውን ሁሉ በአክብሮት እናገለግላለን።

2.2 ሁለተኛ የሰውን እኩልነት እናረጋግጣለን። አባይ በሆን ሚዛንና በአድልዎ አንዱን አክብረን፥ ሌላውን በመናቅ እጃችንን አናከብድበትም። ሁሉንም በእኩልነት በማየት በቅንነትና በየዋሃት እናገለግላለን።

2.3 ሦስተኛ የሰውን ኃላፊነት እናስረግጣለን። ምክኒያቱም እግዚአብሔር እንደ ጠራን ጥሪ መጠንና እንደ ተቀበልነውም አደራ በፍቅር ሕዝቡን በማገልገል የክርስ ቶስ አካል እየጎለበተ፥ እያደገና፥ እየደመቀ እንዲሄድ ለእርሱ በዓላማ እንነሳለን። በአንፃሩ ግን የራሳችንን አጀንዳ፥ ውስጣዊ የሥጋ ፍላጎት፥ የማይሞት "አምላክ የመሆን ጉጉት" በመፀየፍ፤ በፆምና በፀሎት፥ ለጌታም ቃል በመታዘዝ እንዲሚሸሽ በትጋት ልባዊ ውሳኔ እናደርጋለን።

2.4 <u>የእኛ ተመልካች ከብዙኃኑ ሕዝብ፥ ወይንም ከራሳችንም ይልቅ፤ አንድ እግዚአብሔር ነው። እርሱም ሥላሴነት ያለው እግዚአብሔር፦ እግዚአብሔር አብ ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እንደሆነ በመገንዘብና በማወቅ በፊቱ ተጠያቂ ሆነን እንመላለሳለን</u>!!!

**3. የእግዚአብሔር መልክ/ ምሳሌና የሰው ውድቀት፦**

3.1 አሁን ያለን ሁኔታ በአንድ በኩል በእግዚአብሔር አምሳልና መልክ መፈጠ ራችንን፥ በሌላ በኩል ደግሞ በኃጢአት የወደቅን ፍጥረቶች እንደሆንን የሚገልፅ ነው።

3.2 እኛነታችንን ልንክድ፥ ልንጥልና፥ ልንሰቅል የሚገባን በኃጢአት የወደቀ ው "እኔነታችንን" ነው። ይህም ማለት ከክርስቶስ ሐሳብ ጋር የማይሄደውንና በውስጣችን ያለው ክፉ ባህርያችን በሙሉ መሆን ይኖርበታል።

3.3 በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን እኛነታችንን ግን ልንወደውና ልናከ ብረው፥ በውስጡም ያለው ከክርስቶስ ሐሳብ ጋር የሚስማማውን ስብዕናና ባህርይ በሙሉ አክብረን በአድናቆት ልንቀበለው ይገባል። የጌታም ቃል፥ ""ነፍሱን ሊያድ ን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነፍሱንም የሚያጠፋ ሁሉ በሕይወት ይጠብቃታል።" (ሉቃስ 17፥ 33) እንዳለው፤ እውነተኛ የሆነ ራስን መካድ፥ ራሳችንን አጥርተን ለማ

የት፥ ለማወቅና ጌታ እንደ ወደደንም ራሳችንን ለመቀበልና ለመውደድ እንድንችል ያደርገናል።

3.4 የሞራልና የሥነ ምግባር ተጠያቂነት እንዳለብንና የእግዚአብሔርንም ቃል ለመጠበቅና ለማወጅ ኃላፊነት እንዳለብን አስረግጠን ለናምንና ለንቀበለው የሚገባ እውነት ነው።

3.5 የክርስቶስን አካል፥ ማለትም አዲሱ ሕብረተ ሰብ የሆነችው ቤተ ክርስቲያ ንን የክርስቶስ ሙሽራ እንድሆነች በመገንዘብ ለማክበር፥ ለመቅረፅና ለማሳደግ እን ደ ተጠራን ፥ ለዚህም ባለ አደራ እንደ ሆንን አጥብቀን ልናስተውል ይገባል።

3.6 እግዚአብሔር ለሰጠን የፀጋም ይሁን፥ የተፈጥሮ ስጦታዎች፤ ጊዜና ዘመን፤ ገንዘብና ንብረት፤ እና የሰዎችም ሀብት ባለ አደራዎች/ መጋቢዎች መሆናችንን በሙሉ ልብ ልንገነዘብ ይገባል።

3.7 ሰብዓዊ ግልብነታችንን፥ ሞራላችንን የሚያበላሽ ነገራችንን፥ ክፉ የሆነ ባሕርያችንን፥ የተሰጠን የጸጋ ስጦታዎችንም እንዳናሳድግ የሚያግደን ስንፍናችንን ፥ ግለኝነታችንንና እኔነታችንን፥ ሌላውን ወንድማችንን ወይም እህታችንን እየጎዳ ያለውን የበቀል ስሜታችንን በመካድና በመጸየፍ፥ በንስሀም ወደ ጌታ በመመለስ በራሳችን በመጨከን ልንነሳ ይገባል።

### 4. ትክክለኛ ተጠያቂነት፦

4.1 _ለእግዚአብሔር ተጠያቂዎች ነን።_ ምክኒያቱም በቀኑ መጨረሻ መገዛት ያለብን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ስለሆነና፥ ለሌሎች ሰዎች በታማኝነት መመለስ ያለብንም እርሱን ደስ ለማሰኘትና ለማክበር ካለን ውሳኔ የተነሣ ስለሆነ ነው።

4.2 _ለቤተሰባችንም ተጠያቂዎች ነን።_ ከጌታ ቀጥሎ ለሚስታችንና ለልጆቻች ን ተጠያቂነት ሊኖረን ይገባል። ምክኒያቱም ከማንም ሰው ይልቅ እውነተኛው ማንነታችን የሚያውቁትም ሆነ፥ በቅንነት ሊያቀኑን የሚችሉት እነርሱ ናቸው።

4.3 _ለክርስቶስ አካልም ተጠያቂዎች ነን።_ ምክኒያቱም ከጌታ የተሰጠን የመሪነ ት የጸጋ ስጦታዎች (ፓስተርነት፥ ሽምግልና፥ ዲቁና፥ ወዘተ) ለሕዝቡ ሲል የተቀበ ልነው ስለሆነና፥ የተጠራንለትም ሕዝብ ስለሆነ ለእነርሱ ተጠያቂዎች ነን። (ኤፌ. 3:2፤ ቆላ. 1:25)

4.4 *አብረውን ለሚያገለግሉ መሪዎች ማለትም፥ ለፓስተሮች ለሽማግሌዎች፥ ለዲያቆናት፥ ለአገልግሎት ዘርፍ መሪዎች፥ ለቤተ እምነት መሪዎች፥ ወዘተ. ተጠያቂዎች ነን፡፡* ምክኒያቱም አብረውን የሚያገለግሉ መሪዎች ናቸው እንዳንፋንንየሚረዱን፡፡ እግዚአብሔር የሰጠን የመሪነት ስጦታ በአጭሩ እንዳይቀጭና ቀጣይነት እንዲኖረው፥ ራሳችንንና የእግዙአብሔርንም ሕዝብ እንዳንጐዳ ይጠብቁናል፡፡

4.5 *ለትልቁ የክርስቶስ አካልም፥ ማለትም የአማኞች ሕብረተሰብም ተጠያቂዎች ነን፡፡* ምክኒያቱም በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም በአንዲት ቤተ እምነት የምናሳየው አመራር በትልቁ የክርስቶስ አካል አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያመጣ ስለሚችልና፣ በተጨማሪም በየትም ቦታ ያለ የክርስቶስ አካል በእኛ ሕይወትም ሆነ ፥አገልግለሎት ስለሚያገባው ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ፡- "...የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ..." (ኤፌ. 2፡19) እንዳለው የክርስቶስ አካል አንድ ቤተሰብ ነው!

4.6 *ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ላለው አማኝ ያልሆነ ሕብረተ ሰብም ተጠያቂዎች ነን፡፡* በእውነትና በፅድቅ በቅድስናና በፍቅር መኖራችን ከሩቅ ሆነው የሚያዩና የሚታዘቡ፥ ስብከታችን ከኑሮአችን ጋር ከተስማማ ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚመጡ ተቃራኒና የማይጣጣም መሆኑን ሲያዩ ደግሞ ከክርስቶስ ሊርቁ የሚችሉ እነርሱናቸው፡፡ (ፊል. 2፡14-15፥ 1ጴጥ. 3፡15-16)

4.7 *በራሳችን ፊት ለሕሊናችንም ተጠያቂዎች ነን፡፡* እውነቱን እያወቅን ሕሊናችንን በመደለል በየጊዜው የሚወቅሰንም የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ በመናቅና በመሰርጉድ ልናገለግል አንችልም፡፡ የልባችንን ድንግልናና ንጽሕና ለመጠበቅ ለራሳችንም ተጠያቂዎች ልንሆን ይገባል፡፡

5. ወሳኝ የሆነ የሥነ ምግባር መለኪያ፡-

በአመራር የተቀመጡ መሪዎች ሁሉ የላቀና የከበረ ባለ አደራነትና ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት ለማገልገል ከፈለጉ ከሚከተሉት ውድቀቶች ራሳቸውን ሊጠብቁ ይገባል፡፡

5.1 ጊዜኤቸውንና ዘመናቸውን በከንቱ ከማሳለፍ፣

5.2 ሥልጣናቸውን ያለ አግባብ ከመጠቀም፣

5.3 የራሳቸውን ውስጣዊ የሥጋ ረሃብ ከማርካት፣

5.4 ሞራላቸው እንዲበላሽና እንዲላሽቅ ከመፍቀድ፣

5.5 በአገልግሎት ከመወጠር፥ ከመጐዳትና ከመክሰም፡፡

**6. ሦስት አስፈላጊና ወሳኝ ሥነ ምግባሮች፡-**

**6.1 ተጠያቂነት፡-** እንደ መሪዎች ሁላችንም ለሆነ ሰው/ ሰዎች ተጠያቂ ልንሆን ይገባል። አራት ዓይነት ሰዎች ሊኖሩን ይገባል ብዬ አምናለሁ፡-

6.1.1 <u>የልብ ጓደኞች፥</u>

6.1.2 <u>ደጋፊ ቡድን (SUPPORT GROUP)</u>፥

6.1.3 <u>አሰልጣኝ የሚሆነን የእግዚአብሔር ሰው (COACH)</u>፥ እና

6.1.4 <u>የጥበብና የእውቀት መዛግብት የምንቀዳባቸው የተከበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች (MENTORS)</u>!!!

በእነዚህ ሰዎች ፊት በምንሆንበት ጊዜ ዋናው ዓላማችን የውስጥ ስሜታችንን በግልፅነት፥ እውነተኛነት በሞላበት መንፈስ፥ የምንታገልባቸውን ፈተናዎች ለመግ ለፅና፥ በግላችንም ሆነ በመንፈሳዊ እድገታችን እያጋጠሙን ያሉትን ችግሮች ለማካ ፈል ነው። <u>እንዲህ ማድረጋችን ተጠያቂነት ያለው ሰው መሆናችንን ብቻ ሳይሆን፤ ሰው መሆናችን እና መንፈሳውያን እንጂ መንፈስ እንዳልሆንን፤ የመለኮት ባሕርይ ያለን እንጂ፤ መለኮት እንዳልሆንን ያሳያል</u>!

**6.2 ኃላፊነት፡-** በአመራር ያለን መሪዎች የሕይወት ቅደም ተከተላችንን ማስተ ካከል ይኖርብናል። <u>**በመጀመሪያ ተቀዳሚ ሥፍራ እግዚአብሔር፤ ሁለተኛ ቤተሰብ፤ ሦስተኛ በቤተ ክርስቲያን፥ ማለትም በትልቁ ቤተሰብ ውስጥ ያለን አገልግሎት**</u>!!! የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እየበዛ በሚሄድበትና የእኛን ጊዜ ከአግባብ በላይ ሊጠ ይቅ በሚጀምርበት ጊዜ ቆም ብለን ማሰብና ማስተዋል ያለብን እግዚአብሔር በአደ ራነት የሰጠንን የራሳችንን ቤተሰብ (ሚስታችንና ልጆቻችንን) በመጣል ልናደርገው አንችልም፤ አይገባምም። ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት ቀጥሎ፥ ሁለተኛው ኃላፊነታችን ለግላችን ቤተሰብ ነው!!!

**6.3 ወጥነት (INTEGRITY) ፡-**

በቅድሚያ ልናስበው የሚገባን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሥልጣንና ኃይል እን ዴት መጠቀም አለብን? ባለ አደራነትና ተጠያቂነት እንዳለው ሰው እንዴት መለማ መድ አ ለብን? ከርኅራኄና ከንፁህ ፍቅር ጋር፥ ወይንስ የራስን ማንነት መገለጫ በማድረግ ሥጋዊ አሠራር? በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሔር ያስቀመጠን የመሪነት ቦታ ላይ በምናገለግልበት ጊዜ፥ የሥልጣንና የኃይል አጠቃቀማችን ምን ያህል እ ውነተኝነት፥ ክፍትነትና፥ ግልፅነት ይታይበታል? የሚለው ነው። <u>ይኸ ተጠያቂነት ያለውእውነተኝነት ሥልጣንንና ኃይልን ስንለማመድ የምናሳየው ፍትሃዊ አሠራር</u>

በምንገልጸው ጸጋ የተሞላበት አገላለፅ፥ ለእግዚአብሔር በምናሳየው ቅንነትና ቅንዓ ት፥ እናየሰዎችንም ምሥጢር ለመስማትና ለማወቅ የተሰጠንን ዕድል ("PRIVILEG E AND PRIVILEGE INFORMATION") ባለን ምሥጢርን የመጠበቅ አቅምና ዲሲፕሊን ውስጥ ይገለጻል!!!

7. ሥነ ምግባራችንን ለመገምገም የሚረዱ ጥያቄዎች:-

- ከሰዎች ጋር ዛሬ በነበረኝ ጊዜ እውነተኛ ነበርኩ ወይ?
- ከተቃራኒ ፆታ ጋር የነበረኝ ጊዜ ጥንቃቄና ንፅህና የተሞላበት ነበረን?
- የረከሱና ያደፉ ሐሳቦችን፥ የዝሙት ስዕሎችን፥ ስለ ሌሎች ሰዎች መራራ የሆኑ ስሜቶችን አስተናግጃለሁን?
- የገንዘብ አያያዜና አወጣጡ እንደ ባለ አደራ ነበረ ወይ? ንፅህናውን የጠበቀ አጠቃቀም ነበረን?
- ከጌታ የተቀበልኩትና ቤተ ክርስቲያንም የሰጠችኝን አደራ ያለ ማመቻመች በሚገባ ተወጥቻለሁ ወይ?
- የራሴን ውስጣዊ መነሻ ሳልመረምር ለረዥም ጊዜ ወይም በውጥረት አገልግያለሁን?
- የቤተሰቤ "ፓስተር" እኔው እንደሆንኩ በማስተዋል መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ተንከባክቤአልሁ ወይ?
- የራሴንስ መንፈሳዊ ሕይወት አካሄዴ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሆን ለማድረግ በየቀኑ አድርጌአለሁ ወይ?
- ንስሃ ያልገባሁበት ኃጢአት፥ ወይም ይቅርታ ያልጠየቅሁበት ጉዳይ (ቁስል) በውስጤ አስተናግጄአለሁ ወይ?

## 8. ተጠያቂነትን ለማፅናት:-

8.1 <u>ተጠያቂነትን በደስታ መቀበል</u>:- ሰዎች ሐሳብ በሚያቀርቡበት ጊዜ ግትርነትን ማስወገድና፥ ይልቁንም ለሌሎች ምክር ክፍት መሆንን ቀጣይነት ባለው መንገድ መለማመድ::

8.2 <u>ተጠያቂነትን ሞዴል ማድረግ</u>:- ሌሎችን ተጠያቂ አድርጎ ለመያዝና እነርሱን ም ለመጋፈጥ፥ አንዳንዴም መራራ እውነት ከፊቅር ጋር ማቅረብን ሊጠይቅ ይችላ ል:: በዚያውም እኛን እንዴት እድርገው ተጠያቂነት ያለው መሪ ሊያደርጉን እንደ ሚችሉም ለሌሎች ሞዴል ይሆናል::

8.3 <u>ተጠያቂነትን ለማስተማር ዕድሎችን መጠቀም</u>:- ምን እያደረግን እንዳለንናለ ምን እንደምናደርገው፥ ለምንጋፈጣቸው ነገሮች መመሪያዎችን ምን እንደሆኑ እናስ ተምራለን::

8.4 <u>ምንም ጊዜም ቢሆን የሰውን ውስጣዊ መነሻ</u> (MOTIVE) <u>አለመጠየቅ</u>:- ምክኒያ ቱም ስለዚህ ጉዳይ ሙሉ እውቀት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እዚህ ላይ በሁለ ት ነገሮች መካከል ለዩነት ማምጣት አለብን:- "መንፈስን በመለየት" (DISCERN MENT) መካከልና "ፈራጅ" (BEING CENORIOUS) በመሆን መካከል በመሆን መካከል ብዙ ልዩነት አለ:: "መንፈስን መለየት" የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመጠቀ ም በተቀደሰ አዕምሮ የነገሮችን ሂደት መመርመር ሲሆን፤ "ፈራጅ መሆን" ግን ድፍ ን ባለ መልክና በጥላቻ በሰዎች ላይ መለደፍን፥ መፍረድን፥ አንቋሸሾና አሳንሶ ማየ ትን ያመለክታል:: "ፈራጅ" ሰው በሰው ውስጥ ያለውን ክፉ ነገር ብቻ ፈላጊ፥ የው ስጥ መነሻቸው በጎሪጥ የሚያይ፥ እየተከታተለም በእነርሱ ላይ ቀዝቃዛ ውሃን የሚያ ፈስና፤ ለማነነታቸው የማይገደው፥ የአቀራረብ ፀጋም የሌለው፥ ራሱንም በእግዚአብ ሔር ቦታ ማስቀመጡ ብቻ ሳይሆን፥ "እግዚአብሔር ለመሆን የሚጥር"፥ ለእግዚ አብሔር ብቻየተሰጠውን ሥልጣን ያለ አቅሙና መብቱ ለመጠቀም የሚቋምጥ፥ ሌሎችን በፈረደበት ጉዳዮች ራሱ በጌታ ፊት ቢመዘን ተፈትኖ ሊወጣ የማይችል ነው:: (2ቆሮ. 10፥ 17-18)

## 9. በመቅረብና በመለየት መሃል ሚዛንን መጠበቅ:-

9.1 ፓስተሮችና መሪዎች "እየታዩ የማይታዩ መሪዎች"(VISIBLLE- INVISIBLE)

እንዲሆኑ በዓላማ ሊነሡ ይገባል።

9.2 ፓስተሮችና መሪዎች ምን ያህል ወደ ሕዝቡ መቅረብ እንዳለባቸውና፥ ምን ያህ ል ደግሞ ሊርቁ እንደሚገባቸው በማወቅ ሚዛኑን ሊጠብቁ ይገባል። ፓስተሮችና መሪዎች ወደ ሕዝቡ በጣም በሚቀርቡበት ጊዜ በጨዋታ፥ በንግግር ብዛት፥ በሐሜ ታ፥ በቀልድና በቧልት ራሳቸውን ለመቆጣጠር ስለሚሳናቸው፤ የተሰጣቸውን የአገልግሎት ቢሮ ካለማክበራቸውም በላይ፥ መሪውን ከሚመራው ሰው ለመለየት ያዳግታል። ሕዝቡም ከሚያከብራቸው ይልቅ፥ እየናቃቸው ይሄዳል። በአንፃሩም ፓስተሮችና መሪዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ ከፑልፒት ብቻ የሚያውቃቸው፥ "የማይቀረቡና የማይደፈሩ" በሚመስሉበት ጊዜና፤ ምዕመኑን በጅምላ ብቻ እንጂ፥ በየግሉ ሳያውቁት ሲቀሩ፥ ሕዝቡም ከልቡ እያራቃቸውና እያስወጣቸው መሄዱ የማ ይቀር ነው። ስለዚህ ፓስተሮችና መሪዎች በመቅረብና በመራቅ መሃል ሚዛናቸውን መጠበቃቸው አገልግሎታቸው ሞገስ እንዲያገኝና እንዲከበር ያደርገዋል።

9.3 እጅግ የሚያሳስበኝ ደግሞ የአንዳንድ ፓስተሮችና መሪዎች ብቸኝነት በማይበ ት ጊዜ ነው። እነርሱ ራሳቸው ከቅዱሳን ሕብረት እያገለሉ ይሁኑ፤ ወይንም የእግዚ አብሔር ሕዝብ ከሕብረቱ አርቆአቸው ይሁን እርግጠኛ መሆን አንችልም።

9.4 በየትኛውም አቅጣጫ እንውሰደው፥ መነጠላቸው ግን ጤነኝነት የሌለው ከመሆኑም በላይ፤ አደገኛም ነው።

9.5 ፓስተሮችና መሪዎች ያላቸውን ወጥነት ለመጠበቅ በክፍትነትና በመስጠት መሃ ል ያለውን ውጥረት በጥንቃቄ በመያዝ፥ አንዱ ለሌሎች ተጠያቂ የሚሆንበት መለ ኪያ ማበጀትና፤ በክርስቶስ አካል ውስጥ አንዱ ስለ ሌላው የሚገደውና ኃላፊነትም እንዳለው ሊያስተውሉ ይገባቸዋል።

## IV. የባለ አደራነትና ተጠያቂነት እሳቤ፡-

### ሀ. የባለ አደራነትና ተጠያቂነት አንድምታ፡-

1. በቤተ ክርስቲያን አመራር የሚያገለግሉ አገልጋዮች ሁሉ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ለመሰልጠንና ለብቻቸው ለመቆም ከመፈለግ ሊወጡ ይገባቸዋል።

2. የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሁሉ "የተከፈተና የሚነበብ መጽሐፍ" በመሆን ፥ የግል ኑሮአቸውም ሆነ፥ የአገልግሎት ሥምረታቸው ለማንም ሰው በሐቀኝነት ለመግለፅ መፈለጋቸው በጣም ወሳኝ ነው።

3. አገልግሎታቸው ሌሎችን አገልጋዮች የሚያካትት ይሆንና፥ "ሌላነትን" በመቀበል ፀጋቸውን እንዲያሳድጉ በቂም ነገር ሥፍራን የሚሰጥ ሊሆን ይገባዋል።

4. ፓስተሮችና መሪዎች በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ያለውን እምቅ ስጦታ ፈልቅቀው ለማውጣት፥ ለማሳደግና፥ ለመጠቀም የአገልግሎታቸው ዓላማ በማድረግ አዳዲስ ራዕዮችን በየጊዜው ሊቀበሉ ያስፈልጋቸዋል።

5. ፓስተሮችና መሪዎች ቢያንስ በዓመት አንዴ ወይም ሁለት ጊዜ የገንዘብ አወጣጣቸው በውስጥና በውጭ የሂሳብ መርማሪዎች የታየና የተረጋገጠ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በቃልና በፅሁፍ መቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

## ለ. የባለ አደራነትና ተጠያቂነት ውጤት:-

1. በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ ከሥልጣንና ከኃይል እርከን ይልቅ፤ በሚዛን የመጠባበቅ መመሪያ መኖሩን ማረጋገጥ።

2. በግለሰቦችና በአንዳንድ ቡድኖች ያተኰረ አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ፤ በክርስቶስ አካል (ማለትም በጠቅላላው የእግዚአብሔር ሕዝብ) ላይ ያተኰረ አገልግሎትን መስጠት።

3. የእግዚአብሔር ሕዝብ በሙሉ የሚያሳትፍ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓላማ፥ መመሪያና፥ አሠራር ለመወያየትና ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖረው በየጊዜው ማድረግ።

4. መመስገን ካስፈለገ አመራሩ ብቻውን በተናጠል ሙገሳውን ለመቀበል ከመፈለግና እንዲሆንም ከማድረግ ይልቅ፤ ለሌላውም እግዚአብሔርን በመፍራት፥ ነፍሱንም በመግዛት የሚኖረውን፥ ቤተ ክርስቲያኒቱንም በፀሎት የሚደግፈውን፥ በታማኝነትና በመስዋዕትነትም አሥራቱንና በኩራቱን በመስጠት ጌታን እያመለከ ያለውን፥ ለመንፈስ ቅዱስ አሠራርና ለእግዚአብሔር ቃል ልቡን በማስናዳት የሚመጣውን የእግዚአብሔር ሕዝብም ሊመሰገን ይገባዋል።

5. በአገልጋይ መሪነት፥ በባለ አደራነትና፥ በተጠያቂነት ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማገልገል የመሪዎችን ክብር ከሚያደብዝዝ ይልቅ፣ የበለጠ እየደመቁ እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል።

6. ፓስተሮችና መሪዎች ፀጋቸውና ስጦታቸው ብቻ ሳይሆን፥ እርስ በርሳቸውም ልባዊ በሆነ መሰጠት ሊቀባበሉና ሊደጋገፉ ይገባቸዋል።

7. ፓስተሮችና መሪዎች አንድነትን በልዩነት፥ ልዩነትን በአንድነት ውስጥ በመቀበል ሊያገለግሉ ይገባቸዋል።

8. ፓስተሮችና መሪዎች የግለሰቦችን ልዩ አስተዋፅዖ ሊያስተውሉ፥ በአክብሮትም ሊይዙና፥ በአስፈላጊው ጊዜና ቦታም ሊጠቀሙበት ይገባቸዋል።

9. ፓስተሮችና መሪዎች ከምዕመን ጋር "የጋርዮሽ ሥልጣን" መጠቀማቸው አስፈላጊና ወሳኝ ነው።

## V. የባለ አደራነትና ተጠያቂነት እንቅፋቶች:-

- በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ከመሳተፍ ይልቅ ራስን መቆጠብ/ መለገም ፥ ባይተዋር መሆን፣
- እንደ መሪ ከሣጥኑ ውጭ ከማሰብና ከሚደረገው አሠራር በላይ ለማሰብና አዲስ ራዕይ ለማግኘት ከመናፈቅ ይልቅ፥ በሣጥኑ ውስጥ መቆለፍና ባለው አሠራር መወሰን፣
- በትዕግሥት፥ በጥበብና በማስተዋል የምናደርጋቸውን ነገሮች ከማጤን ይልቅ ለማድረግ መቸኮልና ተጣድፎ በተግባር ማዋል፥ አለ እውቀቱ መተግበር፣
- ከመስማት ይልቅ ማድመጥ፣ ማዳመጥ ምንም ነገር አይጠይቅም፥ መስማት ግን መረዳት፥ ማስተዋል በሌለው ሰው ጫማ እግራችንን ማስገባትና የሰውን ስሜት አስተውሎ ማጤንን ይጠይቃል።

- የሰውን ሁሉ ሐሳብ ለመቀበል አልመፈልግና የሚመቹን የጥቂት ሰዎችን ሐሳብ ብቻ መቀበል፤
- የአዕምሮ ጡንቻ በመጠቀም በምንነጋገርበት ጉዳይ ላይ ምን ያህል እውቀት እን ዳለን በማሳየት ራስን ሁሉን እንደሚያውቅ አድርጎ ማቅ ረብ
- በፉክክርና እልኸ በተሞላ መንፈስ፥ በግትርነት መከራከርና "እኔ ልክ ነኝ፥ አን ተ ስህተት ነህ" በሚል አቀራረብ መቅረብ፤
- እንደ እሳት አደጋ አጥፊ፥ ነገሩን ሳናጤንና ለማሰብ ጊዜም ሳንወስድ ሁልጊዜ ተቃራኒ የሆነ አቋም መውሰድ፤
- በተናጠል በአንድ ሐሳብ ጉዳይ አስቀድመን የጠነሰስነውን ሐሳብ ይዘን በዚያው ላይ ብቻ መድረቅ፤
- የግል አጀንዳ፥ ያልሞተ ሥጋዊ ፍላጐት፥ የክርስቶስን አካል ብቻ ሳይሆን ራሳ ችንና የተጠራንበት ጥሪም የሚጐዳ መሆኑን እያወቅን በዚህ እሥራት ውስጥ መ ጠመድ፤
- የምናስተላልፋቸው ሐሳቦች ከሚሰሙን ጋር የማይጣጣም ወይ ግልፅነት የጎደለ ው፥ ወይንም የማይገባ ዓይነት አነጋገር በመጠቀም ሐሳባችንን ለማስተላለፍ መሞከር፤
- ከራሳችንም ሆነ፥ ከሌሎች ሰዎች እውነትኝነት የጐደለው፥ ከፍ ያለ አጠባበቅ (FALSE EXPECTATION) ይዞ ማገልገል፤
- ከሌሎች መሪዎችና ምዕመን ጋር የግንኙነት ሥምረት እንዲኖረን አለመፈለግ፥ አለማሳደግና የብህትውና ኑሮ መኖር፤
- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያጋጠመንን ችግር፥ ውጥረትና ትግል መስማት ለማይ ኖርበት ሰው መናገርና የቤተ ክርስቲያንን ምስጢር አለመጠበቅ፤

➢ በቤተ ክርስቲያናችን ችግር በሚነሡበት ጊዜ በእርጋታ፥ በፅናት፥ በድፍረት ከመያዝ ይልቅ፥ ወይ እንደ ሰጎን ችግሩን እያየን እንዳላየን መሆን፥ ወይንም እንደ ፈረስ ለመዋጋት መፍጠን፤

➢ እንደ ፓስተሮችና መሪዎች መንፈሳዊ ብስለት ማጣትና ከጌታ የተቀበልነው ሥልጣንና ኃይል መንፈሳዊ እንደሆነ አለማስተዋል:: የሚያጋጥሙንም የቤተ ክርስቲያን ችግሮች ሥጋዊ በሆነ ምላሽ ለመጋፈጥ መሞከር፤ (ዘፍ. 4:1-5፥ 13:1-8፥ 26:12-25፥ 37-50፤ 1ሳሙ 18-19፤ ማቴ. 20: 24፥ ሉቃስ 10: 38-42)

## VI. የልብን ንጽሕናና ወጥነትን መጠበቅ:-

➢ የልባችንን ንፅህናና ድንግልና በየቀኑ መጠበቅ፥ ለእግዚአብሔር መንፈስና ለጌታም ቃል የተከፈተ እንዲሆን ማድረግ፥ (መዝ. 27:4፥8፤ ሮሜ 12:1-21፤ 1ቆሮ13:4-8፥ ኤፌ. 4:25-32፥ ፊል. 2:1-11፥ ዕብ. 12:1-3)

➢ የልባችንንና የሕይወታችን ወጥነት መጠበቅ፤ ተጠያቂነት ያለው ኑሮና አገልግሎት እንዲኖረን መወሰን፤

➢ የግልና የቤተሰብ መንፈሳዊ ሕይወት መነቃቃት፣ ትንቢታዊ የሆነ ኑሮ፥ የወደፊት አቅጣጫ የሚያሳይ አዳዲስ ራዕይ፥ እያደገና እየጋለ የሚሄድ መንፈሳዊ ቅንዓት፥ በሌሎች ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚያመጣ ሕይወት፥ እና መለኮታዊ የሆኑ የጸጋ ስጦታዎች በሕይወታችን እያበቡ እንዲመጡ በንፁህ ልብ መፈለግና መናፈቅ፤

➢ ለጌታም ሆነ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ዋናው ነገር ምንድነው? ብንል፥ የእግዚአብሔር ሰው የልብ ንፅህናና ድንግልና ነው!!! (ዘፀ. 28:30፤ ዘኁ. 12:1-3፤ 1ሳሙ. 16:7፤ የሐዋ. ሥራ 13:22-23፥36፤ ማቴ. 11:29)

➢ ቅድስናና ወጥነት:- በብሉይ ኪዳን "ቶም" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል "ሙሉነት" ማለት ሲሆን በእግዚአብሔርና በራስ ፊት ፍፁም እውነተኝነትን ወይም ሐቀኛ መሆንን ያመለክታል:: ወጥነት ማለት ማንም ታዛቢ፥ ተመልካች ሰው

በሌለበት ቦታና ጊዜ እንኳ ሳይቀር ትክክለኛ ፅድቅ የሆነውን ነገር ማድረግ መቻል ነው።

# VII. ባለ አደራነትና ተጠያቂነት፦ የገንዘብ አያያዝ

## ሀ. የውስጥ ቁጥጥርና የሂሳብ አያያዝ ሥነ ሥርዓት፦

1. የፓስተሮችና የሽማግሌዎች ድርሻ፦ ከዲያቆናት መካከል በኃላፊነት የገንዘብ ቆጠራውን ሂደት የሚያካሂዱ ሁለቱን ወይም ሦስቱን መሾም አለባቸው። ምንም ጊዜም ቢሆን ፓስተሮችና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጥሬ ገንዘብም ሆነ ቼክ ፈጽሞ መያዝ የለባቸውም።

2. በቤተ ክርስቲያኒቱ ለማገልገል ተጋብዘው ለሚመጡ አገልጋዮችም ይሁን፥ ለምንም ለሚከፈለው ሰው በጥሬ ገንዘብ ከመስጠት መታገድ አለባቸው። ሁሉም የገንዘብ አወጣጥ በቼክ መሆን ይኖርበታል።

3. ፓስተሮች አብሮአቸው በቼኩ ላይ የሚፈርም የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌ (ሽማግሌዎች) ከሌሉ በስተቀር ለብቻ ከመፈረምና፥ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ የገባውም ገንዘብ ወደ ባንክ ወስዶ ከማገባትም ራሳቸውን ሊያግዱ ይገባቸዋል።

4. ሁሉም ተከፋይ የሆኑ ወጪዎች በኢንቮይስና ፎርምም ተዘጋጅቶ የአንዱ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ፊርማ ያረፈበት መሆን ይኖርበታል።

5. ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሁለት የባንክ አካውንቶች በላይ (ማለትም አጠቃላይ ፈንድና የሕንፃ ፈንድ) አለመያዟ በጣም አስፈላጊ ነው። አካውንቶች በበዙ ቁጥር ችግሮች መፈጠራቸው አይቀሬ ነው።

6. ለፓስተሮች፥ ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮችና፥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሙሉ ጊዜ የሚሠሩ ሠራተኞች (በአሜሪካ ላሉት) ለአይ አር ኤስ (IRS) መሙላት ያለባቸው W-2 እንጂ ፎርም 1099 መሆን የለበትም። በሌሎች አገሮች ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ እንደ አገሩ ሕግና ደንብ በጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባቸዋል።

7. የቤተ ክርስቲያኒቱ ዳታ ቤዝ (DATA BASE) ማዘጋጀት።

8. በዓመቱ መጨረሻ ላይ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት በአሥራትና በበኩራት፥ በስጦታም መልክ ለሰጡ ሰዎች ሁሉ ደረሰኝ አዘጋጅቶ ለሚጥይቅ ሁሉ መስጠት።

9. የውስጥና የውጭ የሂሳብ ምርመራ ወይም ቁጥጥር ዘዴ ማዘጋጀትና በሥራ መተርጐም።

10. በየወሩ የገንዘብ ወጪ ሰነዶችን ማዘጋጀት፥ ወጪና ገቢውን ማስተያየት፥ በዓመት ሁለት ጊዜ ደግሞ በሂሳብ መርማሪዎች የተዘጋጀ የሂሳብ ሪፖርት ለጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን አባላት ጉባዔ ማቅረብ፤ እንዲጠይቁም መፍቀድና ማስጸደቅ።

11. ሁልጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱን የገንዘብ ኃይል ማጤን።

12 በቤተ ክርስቲያኒቱ የመጣውን ገንዘብ በሙሉ ደረሰኞች የተደገፈና በሥነ ሥርዓትም የተያዘ መሆን ይኖርበታል።

## ለ. ራዕያችን ከገንዘብ አቅማችን ጋር የሚሄድና የገንዘብ አወጣጣችንም ራዕዩን የሚደግፍና የሚያጐለብት መሆን ማረጋገጥ፡-

1. ከራዕዩ ጋር የሚሄድ ባጀት ማዘጋጀት፤

2. የሂሳብ ሰነዶቻችን ከባጀቱ ጋር ማነጻጸር፣

3. የቤተ ክርስቲያኒቱ የገንዘብ አቅም፥ የሚያስፈልጋትም ገንዘብ ለምዕመኑ መናገር፥ መግለፅ፥ የተሰጣቸውን የመደገፍ ዕድል እንዲጠቀሙበት ማበረታታት።

4. “የባለ አደራዎች ቡድን” (STEWARDSHIP TEAM) ማቋቋምና የቤተ ክርስቲያኒቱን የገንዘብ አወጣጥ ንፅህና እንዲጠብቁ ማድረግ።

5. የፓስተሮች የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች “ደሞዝ” ከሚገባ በላይ የተለጠጠ፥ ወይንም እጅግ ያነሰ እንዳይሆን ፍትሐዊ ሊሆን ይገባዋል። ምክኒያቱም የተለጠጠ ሲሆን የሕዝቡን ሕሊና ይጐዳል፤ ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ሕይወታቸውን በመስጠት በማገልገል ላይ ያሉትን አገልጋዮችና ቤተሰባቸውን ከመጉዳቱም ሌላ፥ በየጊዜው

በገንዘብ እንዲፈተኑና ሌላ ያልፈለጉትን ነገር እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ አቅምና እንደ አገሩ የመኖሪያ መለኪያ ከደመወዛቸው በተጨማሪየሕክምና ወጪ፤ የቤት ኪራይ÷ የጡረታ አበል እና የመጓጓዣ ወጪዎች ሊታሰብላቸው ይገባል ብዬ አምናለሁ።

### ሐ. ስለ ገንዘብ ባለ አደራነት ማስተማር፡-

1. ለቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በየጊዜው ስለ ገንዘብ ባለ አደራነት የበሰሉና የነጠሩ ትምህርቶችን መስጠት።

2. የሥራን ክቡርነት በመግለጽ በትጋትና በሐቀኝነት ምዕመኑ በሥራ ሊሠማራ የሚያስችል የሥራ ሥነ ምግባር በተመለከተ የጠለቀ ትምህርቶችን መስጠት።

3. የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የሚያውቁት የሥራ ዕድሎችና ክፍት ቦታዎች ሲኖሩ ኢንፎርሜሽን የሚለዋወጡበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

4. በከተማው ውስጥ የሚሰጡ የሥራ ዕድሎች ሥልጠና ካለ ለሕዝቡ ማሳወቅና እንዲሳተፉም ማበረታታት፤ ቤተ ክርስቲያኒቱም ፕሮፌሽናል የሆኑና እውቀቱ ያላቸውን ሰዎች በመጋበዝ በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ እንዲካሄድማድረግ።

5. በዓመት አንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀ "የገንዘብ ባለ አደራነት ቀን" አዘጋጅቶ ብዙ እውቀት ያላቸውን ሰዎች በመጋበዝ የቤት ግዢ÷ የብድር ካርዶች አጠቃቀም፤ የንግድ አጀማመርና አያያዝ÷ የህክምና ነክ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ሰሚናሮች እንዲሰጡ ማድረግ።

6. በምሳሌነትና ሞዴል በመሆን መምራት፤ በገንዘብ ላለ አደራነት ጉዳይ ንጹሕ የሆኑ እጆችን መያዝ፤ ያለ ነቀፋም መመላለስ።

### መ. የስብከት ባለ አደራነት፡-

1. በሙሉ ልብ መስበክ ፡- በአንድ በኩል እግዚአብሔር በእግዚአብሔር ቃል ብዙ ስለተናገረ፤ በሌላ በኩል የእግዚአብሔርን ሕዝብ የምንወድ ከሆነ ደግሞ እውነቱን ልንነግራቸው ይገባል።

2. በጥንቃቄ መስበክ:- ስለ ገንዘብ ነክ (ጉዳይ) በምንሰብክበት ጊዜ ብዙ ማስተዋል፥ ጥንቃቄና እርጋታ ባለው መንፈስ ልናደርገው ይገባል።

2.1 በመስጠታቸው ሊበለጽጉ እንዳላቸው ከመናገርም መቆጠብ፤ ምክኒያቱም ሐዋር ያው ጳውሎስ እንዳለው:- "*አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ* *<u>የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል</u>።*" የሚለው ቃል የታመነ ነው። (ፊል. 4፥ 19)

2.2 የገንዘብ ችግር ስላለን ብቻ በልመና መልክ ከማቅረብ መቆጠብ፤ ምክኒያቱም የእግዚአብሔር ሕዝብ አካሄዱን በየቀኑ ከጌታ ጋር ለማድረግ ያለውን መሰጠት መግለጫ እንደሆነ ልናሳስበው ይገባል።

2.3 "አሥር ከመቶ ለእግዚአብሔር፥ ዘጠና ከመቶ ደግሞ ለእኛ" የሚለውን አስተሳሰብ ከመስጠት መቆጠብ፤ ምክኒያቱም የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው ሁለንተናችን (እንኳንና ገንዘባችን) የጌታ እንደሆነ ነው። ይህ ማለት አሥራታችን ለቤተ ክርስቲያን አንስጥ ለማለት አይደለም፤ ይልቁንም ከዚያም አልፈን የበለጠውን በደስታና በመስዋዕትነት ልንሰጥ ይገባናል።

3. የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት በማጥናት፥ የምንሰብክበት ቋንቋ ሳይቀር የተቀመመና ጸጋ የተሞላበት፥ ብዙ እንደ ተዘጋጀን በሚገልፅ መልኩ እንጂ፤ ድግግሞሽ የተሞላባቸው ቃላቶች፥ አረፍተ ነገሮች፥ ወይንም ሐሳቦች አለማቅረብ።

4. የመስጠት ነገር ማዕከል ያደረገና ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባ፥ እግዚአብሔርን የመውደዳችን ምልክት፥ የሚገልፅ መግለጫ እንደ ሆነ በማሳየት መስበክ።

5. ቀጣይነት ባለው መንገድ መስበክ:- ቀጣይነት ባለው መንገድ እንጂ ለጆሮ እስኪሰለች ድረስ በድግግሞሽ ልንሰብክ አይገባም። ምክኒያቱም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመታዘብም አልፎ፥ ይሰለቸናል። በተለይም በቤተ ክርስቲያኒቱ ምንም ዓይነት የገንዘብ ውጥረት በሌለበት ወቅት የገንዘብ ባለ አደራነት መስበክ የበለጠ የእግዚአብሔር መንግሥትን ሐሳብ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል።

# ምዕራፍ አሥር

## አመራርና የመግባባት ችሎታ፥

## (LEADERSHIP & COMMUNICATION)

- *"እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፡- ከአገርህ፥ ከዘመዶችህም፥ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፤ እባርክሃለሁ፤ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፤ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።" (ዘፍ. 12፥ 1-3)*
- *"በዚያችም ሌሊት እግዚአብሔር ተገለጠለት፤ እንዲህም አለው፡- እኔ የአባትህ የአብርሃም  አምላክ ነኝ፥ አትፍራ፥ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና እባርክሃለሁ፤ ስለ ባርያዬ ስለ አብርሃም ዘርህን አበዛለሁ" (ዘፍ. 26፥ 23-24)*
- *"እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ በምትሄድበትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ፤ የነገርኩህንም ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና።" (ዘፍ. 28፥ 15)*
- *"በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም። አንበሳው አገሣ የማይፈራ ማን ነው፤ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ፥ ትንቢት የማይናገር ምን ነው?" (አሞፅ 3፥ 7)*
- *"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።" (ዕብ. 1፥ 1-3)*

## I. መግቢያ:-

እግዚአብሔር በባሕርዩ መግባባትን የሚወድ አምላክ ስለሆነ ይናገራል። በዘፍጥ ረት 1፥ 3 ላይ:- "እግዚአብሔርም:- ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ።" በማለት ይጀምራል። ዮሐንስም በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ:- "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ... ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፤ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩ ንአየን።" ይላል። (ዮሐ. 1፥ 1፥ 14) በሥላሴመሃል በዘላለምና በዘመናት ውስጥ እፁብ ድንቅ የሆነ መግባባት አለ። ሦስትነት ያለው እግዚአብሔር:- በእግዚአብሔር አብ፥ በእግዚአብሔር ወልድ፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሃል ልዩ ጣዕም ያለው መግባባት አለ።

ከዚህ ባሕርዩ የተነሳ እግዚአብሔ እኛንም በመልኩና በምሳሌው ሲፈጥረንም መግባባት የምንችልና የምንወድም እንድንሆን አድርጎ ነው የፈጠረን። ምንም እንኳ ን ይኽ በፍጥረት ጊዜ ያገኘነው የመግባባት ፍላጎትና ችሎታ በኃጢአት ምክኒያት ቢበረዝና ቢደበዝዝም፤ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ከራሱ (እግዚአብሔር)፥ ከራሳችን፥ ከእርስ በርሳችንና፥ ከአካባቢያችን ጋር ለመታረቅ የምንችልበት ከሰማይ የተላከ መሰላል (ዘፍ. 28፥ 10-15፤ ዮሐ. 1፥ 51- 52) ሆኖ አስታርቆናል።

ይሁን እንጂ በጸጋ የዳንን ኃጢአተኞች ስለሆንንና በውስጣችንም አዳማዊ ባሕ ርይ ስላለ፤ በመሪዎች (ማለትም:- በፓስተሮች፥ በሽማግሌዎችና፥ በሌሎች አገልጋ ዮች) መካከልም ይሁን፥ በመሪዎችና በምዕመናን መካከል ብዙ ያለ መግባባት ችግሮ ች በየዘመናቱ ሲነሱ ማየት እንግዳ ነገር አልሆነም። የአለመግባባታችን ምክኒያቶች ዘርፈ ብዙ ቢሆኑም፤ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል መንፈሳዊ ብስለትና የሕይወት ለው ጥ ማጣት፥ የባሕርይ ችግር፥ የመግባባት ችሎታ ማጣት፥ በልጅነታችን የነበረን የአ ስተዳደግ ልምምድ፥ ከውስጣችን ያልጠፋ ቁርሾና የበቀል ስሜት፥ የሕሊና ወቀሳና ጸጸት፥ የልብ ትዕቢትና ክፋት፥ ራስን የማምለክ ችግር፥ ሌላነትን ለመቀበል አልመ ፈለግ፥ የሕይወት ብክነት፥ ሳያስተውሉ በችኮላ የመናገር ባሕርይ፥ ሰውን በቅንነት ለመስማት አለመፈለግ፥ ይልቁንም ጸጉር የመሰንጠቅ ያህል ንግግራቸውን ማስተን ተን፥ ወ.ዘ.ተ. የሚሉት ይገኙበታል። ስለዚህ ስለ አለመግባባት ጉዳይ ማየታችን በጣም አስፈላጊ ነው። ምክኒያቱም የመግባባት ጉዳይ በአመራራችን ላይ የሚያመጣ ው ተጽዕኖ ብዙ ስለሆነ ለአገልግሎታችን፥ ይልቁንም ወንጌልን ለማሠራጨት ዋና መሣሪያ በመሆኑ ልናበላሽ፥ ወይንም ልናሳምር እንችላለን።

## II. የመግባባት ተግዳሮቶች:-

በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ ያለነው መሪዎች ሁሉ በዚህም ይሁን በዚያ የወንጌል አገልጋዮች ስለሆንን በየጊዜው ልንጠይቃቸውና ምላሽ ልናገኝ ላቸው የሚገቡን ጥያቄዎች እንዳሉ መገንዘቡ ለብዙ ነገር ይረዳል ብዬ አምና ለሁ::

1. የማገለግለው ሰው ወይንም ሕዝብ የምናገረው ነገርና ለማስተላለፍ የፈለግሁትን መልዕክት ይሰማል ወይ? ካልሰማስ ለምን?

2. የክርስቶስን ወንጌል በትክክል ለሚገባቸው ሰዎች፥ ሊገባቸው በሚች ል ቋንቋና ወቅታዊ በሆነ መልክ አስተላልፋለሁ? ወይንስ የተቀየጠ፥ ግልፅነት የጎደለው፥ የተሸራረፈ ወንጌል፥ ወይንም ደግሞ ለሰው ጆሮ እንዲጥም ብዬ የተመቻመቸ ወንጌል እሰብካለሁ ወይ?!

3. በእኔና በእግዚአብሔር ጉባዔ መካከል፥ በእኔና የምሥራቹን ወንጌል በምሰብክለት ዓለም መካከል ለምን አልመግባባት ተፈጠረ? ይኸንን ግድግዳ እንዴት ላፈርሰው እችላለሁ?

4. የማገለግለው ጉባዔ፥ ወይም ዓለም በቅርበትና በጥልቀት አውቀዋለሁ ወይ? ወይንስ አላውቀውም?

5. ለእግዚኤብሔር ሕዝብና ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ላለው ዓለም ልብ ውስጥ በሚገባና የተሰጠኝን የወንጌል አደራ በሥልጣን እንዴት ዘላለማዊነት ያለው ቃል ማስተላለፍ እችላለሁ?

እነዚህ ጥያቄዎች በእውነት የወንጌል አገልጋይ ለሆነ ሰው ብዙ የሚያሳስቡ፥ ምናል ባትም የሚረብሹና ዘላቂነት ወዳለው ፈውስና መፍትሔ የሚያመጡ ናቸው:: አሁን ያለው ጥያቄ ይኸ የማይለወጠውን የክርስቶስን ወንጌል በየዘመኑ ተለዋዋጭ ለሆነው ትውልድ አቅርቦታችን እንዴት ሊሆን ይገባዋል? የሚለው ነው:: ይኸንን ጥያቄና ሌሎችንም ለመመለስ እንዲረዳን አንዳንድ የመግባባት ሞዴሎች ማየታችን አስፈላጊ ነው::

## III. "የሻነን-ዊቨር የመግባባት ሞዴል"

### ሀ. "የሻነን-ዊቨር ሞዴል" ጥቅም:-

"የሻነን-ዊቨር የመግባባት ሞዴል" "የሞዴሎች ሁሉ እናት" በመባል ይታወቃል::[385] ይህ የመግባባት ሞዴል ለመጀመሪያ ጊዜ ያጠናው ክላውዴ ሻነን የሚባለው ሰው (እ.አ.ዘ.አ. 1948 ዓ.ም.) ነው::[386] በኋላም ዋረን ዊቨር ከሚባለው ጸሐፊ ጋር ሆነው "በኢንፎርሜሽን ቲዮሪ" ላይ መጽሐፍ ጽፈዋል::[387]

"የሻነን-ዊቨር የመግባባት ሞዴል" ሁለት ጥቅሞች አሉት:: አንደኛ ሊተላለፍ የተፈለገው የመልዕክቱ ንፅሕና (ጤንነት - "FIDELITY") ላይ የሚያተኩር ሆኖ፣ መልዕክት ተቀባዮቹ እንዴት እንደተቀበሉትና እንደተረጎሙት፥ ሊተላለፍ ከተፈለገው ሐሳብ ጋር አቀባበላቸውና አተረጓጐማቸው ምን ያህል እንደሚሄድ ያሳያል:: ሁለተኛ የመልዕክቱን ንፅሕና ሊያውክና ሊያበላሽ የሚችለውንም ድምፅ ወይም የድምፅ ሞገድ ("NOISE")አጥርቶ ያሳያል:: ስለዚህ ይህ ሞዴል ልናስተላልፍ የሚፈልገውን የወንጌል እውነት ሳይበረዝና ሳይጭበረበር፥ ሊደርስለት ለሚገባው ሕዝብ ሊገባው፥ ሊቀበለውና፥ በትክክል እንደተፈለገው ሊተረጉመው እንዲችል፥ በሕዝቡም ሕይወት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የወንጌል መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቅማል::

### ለ. "የሻነን-ዊቨር የመግባባት ሞዴል" ሂደት:-

**1. የመልዕክቱ ምንጭ:- ("SOURCE")**

ለእኛ ለክርስቲያኖች የመልዕክታችን ምንጭ ወንጌል፥ ማለትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 1፥ 1-4 ላይ እንዲህ ያላል:- "*ይህምወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ፥ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠው ስለ ልጁ ነው፤ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::*" ከእርሱም በተጨማሪ ሌላው ምንጭ የእኛ የክርስቲያኖች እንደ ግለሰብና እንደ አዲሱ ሕብረተ ሰብ የምንኖረው ኑሮ ነው:: የመጀመ

---

385 David D. Woods and Erik Holinagel, *Joint Cognitive Systems: Foundation of Cognitive Systems Engineering,*, (Boca Baton, FL: Taylor & Francis, 2005).
386 Claude Shannon, *"A Mathmatical Theory of Communication," Bell System Technicla Journal* 27 (July and October, 1948): 379-423.
387 Warren Weaver and Claude Elwood Shannon, *The Mathmatical Theory of Communication,* (Chicago, IL: University of Illinois Press, 1963); See also Sergio Verdu, *"Fifty Years of Shannon Theory," In* Sergio Verdu and Steven W. McLaughin, *Information Theory: 50 Years of Discovery*, (.p: IEEE Press), 13-34.

ሪያው ዋና ምንጭ እግዚአብሔር ሆኖ፥ የእኛ ሕይወትና ኑሮ በሁለተኛ ደረጃ ሊታ ይ የሚገባ ነው:: ስለዚህም እንደ አገልጋዮች ይሁን፥ እንደ ምዕመን የምናስተላልፈ ው መልዕክት አስቀድሞ እግዚአብሔር በልጁ በኩል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሰጠ ን ስለሆነ ነው:: የመልዕክቱ ባለቤትና አውራም እግዚአብሔር ነው::

በማስተዋል ልብ ብለን ልናጤነው የሚገባን መልዕክቱም ይሁን፥ መልዕክተኛ ውም እኛ አይደለንም:: መልዕክቱም ሆነ፥ መልዕክተኛውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ ነው!!! እንደ አገልጋዮች የእኛ ሥራ ይኽ መልዕክትና መልዕክተኛ የሆነውን ጌታ ለሰዎች ማስተናገድ፥ መግለጽና፥ ማወጅ ነው!!!

2. መልዕክቱን የማስተላለፊያ መንገድ:-

("ECODING/ TRANSMITTING")

እግዚአብሔር ለሕዝብ ሁሉ ደህንነት እንዲሆን በማሰብ በሁለት ዋና ነገሮች ራሱን ገልጧል:: አንድም "በጠቅላላ መገለጥ" (GENERAL REVELATION) ፥ ማለትም በሰው ውስጥ ያስቀመጠው የሕሊና ሚዛን (ሮሜ 1፥ 18-32)፥ እና እጁ በሠራቸው ፍጥረታትም በኩል (መዝሙር ዳዊት 8፥ 1-9፥ 19፥ 1-6) ጌታ እግዚአ ብሔር ማንነቱን ገልጿል:: አንድም ደግሞ "በልዩ መገለጥ" (SPECIAL REVELATION)፥ ማለትም በነቢያትና በሐዋርያት ቃልና (ኤፌ. 2፥ 2021፣ ዕብ. 1፥ 1)፥ በመጨረሻም በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ተነገረን:: (ዕብ. 1፥ 1-3)

ይኸንን ክቡር ወንጌል በአደራነት የተቀበልነው እኛ አገልጋዮች ደግሞ የወንጌ ሉ መልዕክት ሳይሸራረፍ፥ ሳይቀየጥና፥ ሳይመቻመች የምሥራቹን ወንጌል ሊሰማ ወደሚገባው ሕዝብ በልብ ንጽሕናና ቅንነት በተሞላው መንፈስ፥ በትሕትናና በድፍ ረት፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለቃሉ የሚገባ በጸጋ የተቀመመ ንግግር መልዕክቱን ማስተላለፍ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሕዝቡ ይጠበቅብናል:: ይህም ማለት መልዕክቱ ን ለማስተላለፍ የምንጠቀምበት የቋንቋና የንግግር ዘይቤ፥ ከእኛ ደረቅ አዕምሮ አስ ተሳሰብ፥ ወይንም የስሜት ግልቢያ በተለየ ሁኔታ በእርጋታ፥ በእርገጠኝነትና ቅንነ ት በተሞላበት መንፈስ ሊተላለፍ ይገባዋል:: የወጌልን መልዕክት የማስተላለፋችን ዋና ዓላማው እግዚአብሔርና ሕዝቡ ዓይን ለዓይን እንዲተያይ ሁኔታን ማመቻቸትና የጌታንም ስም እንዲከበር ማድረግ ነው:: (2ተሰ. 3፥ 1-2)

3. የድምፅ ሞገድ ("NOISE") ፥

እንደ እግዚአብሔር ሰዎችና የወንጌል አገልጋዮች ሁልጊዜ ማሰብ ያለብን የመ ልዕክቱ ንፅህና እንዴት መጠበቅ እንደምንችል ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ "በወንጌል

*አላፍርምና ... ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና::"* (ሮሜ 1÷ 16) እንዳለው ነው:: ነገር ግን ይኸንን ክቡርና ንፁህ የሆነውን የክርስቶስ መልዕክት በስብከት÷ በማስተማር÷ ለግለሰቦች በመመስከር÷ ወ.ዘ.ተ. ለማስተላለፍ በምንሞክር በት ጊዜ መልዕክቱ ለሰሚዎቹ በትክክል እንዳይሰማ የሚያደርግ የድምፅ ሞገድ መኖሩ የማይካድ ሐቅ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ የድምፅ ሞገድ ልናስተላልፈው የፈለግነ ውን መልዕክት ሊያደበዝዝ÷ ሊያቆራርጥ÷ ወይም በሌላ እንዲተረጉሙት ሊያደርግ ይችላል::

የድምፅ ሞገድ የማይፈለግ አቆራራጭ የሆነ ምልክትና የመልዕክቱንም ንፅህና እንዳይጠበቅ የሚያበላሽና በሌላ እንዲተርጉሙት ሰሚዎቹን የሚያስገድድ ማለት ነው:: በጣም ጥሩ በሆነና በጠራ መንገድ እንኳን መልዕክቱን ስናስተላልፍ÷ ካስተላለ ፍነው መልዕክት መካከል በመልካም ተቀባይነት ለተፈለገው ሕዝብ መተላለፍ የሚ ችለው ሰማንያ ከመቶ (80%) ብቻ ነው:: ለሚያጋጥመን የድምፅ ሞገድ ምክኒያት ቢያንስ አራት ምክኒያቶች መኖራቸውን ለመግለፅ እወዳለሁ::

**3.1 የባሕል ድምፅ ሞገድ:- (CULTURAL NOISE)**

የራሳችንም ሆነ የሚሰማው ሕዝብ ከባህላችን ይዘናቸው የመጣናቸው ባህላዊ÷ ግምታዊ÷ የይሆናል አስተሳሰቦች፤ ወይም አሉታዊ÷ የተጭበረበረና÷ የተሳሳተ አመ ለካከት፤ በራሳችን "የዓይን መነፅር" እይታ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ፤ በምንጀር በት ምጊዜ፤ በሴኩላር ዓለም የተለወሰ አስተሳሰብ፤ ወይንም ደግሞ ባደግንበት ባህላ ዊ መረዳት በመነሣት ስንረዳው፤ እግዚአብሔር ሊለው የማይፈልገውን ሌላ ሐሳብ በማስተላለፍ ወይም በመስማት ልንደምድም እንችላለን:: ይህን ዓይነት ጣልቃ የሚ ገባ ድምፅ የመልዕክቱን ዋና ሐሳብ እንዳይተላለፍ ከማገዱም ሌላ÷ ሰሚውም ከእግ ዚአብሔር ይቅርታና ምህረትን እንዳይጠብቅ ሊያግደውና ሊያሰናክለው ይችላል::

**3.2 *ሥነ መለኮታዊ የድምፅ ሞገድ* (THEOLOGICAL NOISE)**

ከቤተ ክርስቲያን መድረክ "እኔ ደህና ነኝ፤ አንተም ደህና ነህ" የሚል መልዕክ ት መተላለፍ ከጀመረ እውነተኛ በሆነው የወንጌል መልዕክት ላይ ውሃ እንደማፍሰስ ይሆናል:: <u>ወንጌል ሁለት ባሕርያት አሉት:- በአንድ በኩል የታወከውንና የተረበሸው ን ሰው በሰላም ሞልቶ ያረጋጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ በመደላደልና በእልከኝነት የተ ቀመጠውን ሰው ያውካል÷ ያናውጣል:: በምንሰጠው የወንጌል መልዕክት ይህ ካልታየ ራሳችንን ልንጠይቅና ልንመረምር ይገባናል!!!</u>

### 3.3 ግላዊ የድምፅ ሞገድ (PERSONAL NOISE)

በግላችን የባሕርይ ችግር ሲኖረን፥ የልጅነት የአስተዳደግ ልምምድ የተነሣ ያልተፈወሱ ቁስሎች ሲኖሩን፥ በሕይወታችን ካለፍንባቸው ችግሮች የተነሣም መራራነትን በውስጣችን ስናስተናግድ፥ የበደሉንን ሰዎች በይቅርታና በምሕረት መቀበል ሲያቅተን የመግባባት ችሎታችንን ሊያበላሸው ይችላል:: የወንጌል መልዕክት አቀራረባችንም ሆነ አቀባበላችን የተበላሸ ሊያደርገው ይችላል::

### 3.4 መንፈሳዊ የድምፅ ሞገድ (SPIRITUAL NOISE)

የእግዚአብሔር ቃል "ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ (ሰይጣን) የማያምኑትን አሳብ አሳወረ::" ብሎ በግልፅ ይናገራል:: (2ቆሮ. 4፥ 4) የወንጌል መልዕክት ለማስተላለፍ በምንም እንዳይሰሙት ሰይጣን አዕምሮአቸውን ያጨልመዋል፤ የማያምኑትንም ሰዎች አሳብ ያሳውራል:: ከግለሰቦች ጋር ያለን የመግባባት መሥመርም አንዳንዴ ሐሳባችንን በማጣመም እንዲሰሙትና፥ ክርስቲያኖችም እንኳን ሆነው በሌላ እንዲተረጉሙት ልናስተላልፈው የምንፈልገውን መልዕክት ሰይጣን በመሃል ሊያቋርጥ ይችላል:: ሆኖም የእርሱን ሐሳብ ሳንስትና በሰይጣን ሳንታለል በጸሎት ኃይል አሠራሩን እያፈረስን የወንጌልን መልዕክት ያለ መታገድ ማስተላለፍ የእግዚአብሔር ልጅነት መብትና ሥልጣናችን ነው!!!

- ❖ ምንም እንኳን የድምፅ ሞገዶቹ ደረጃና ቢጋር በየጊዜው ከሰው ወደ ሰው ቢለያይም፤ የማይለወጠው የተባረከው የክብር ወንጌል መልዕክት በጥራት፥ በብቃት፥ እና የተሰጠንን ዕዳሎት ግምት ውስጥ በማስገባት ልንጠብቀው፥ ልንሰብከውና፥ ልናውጀው ይገባል!!!

## 4. የመልዕክቱ ተቀባይ ("DECODER/ RECEIVER") :-

የመልዕክቱ ተቀባይ መልዕክቱን ከሰማ በኋላ የሰማውን መተርጐምና ለራሱ አዕምሮ ሊገባው በሚችል መንገድ ለመገንዘብና ለመተርጐም በሚያስችለው መንገድ መቀበል ይኖርበታል:: እዚህ ላይ መርሳት የሌለብን የመልዕክቱ ተቀባይ የሆኑ ሰዎች አስቀድመው የጠነሰሱትን የራሳቸውን ሐሳብ ይዘው ማድመጣቸውና መልዕክቱን ሲተረጉሙትም በራሳቸው መነፅር እይታ እንደሆነ ነው:: ነገር ግን ይህንን አልፎና ጥሶ የሰዎችን ልብ የሚነካ የቃሉ ኃይልና የመንፈስ ቅዱስም አሠራር በላጭነት እንዳለው ልናስተውል ይገባል!!! የቃላቶቹ ትርጉም በምንናገረው ቃላት ካለው ይልቅ፤ በእኛ መልዕክቱን በምናስተላልፈውና በሰሚዎቹ ውስጥ ነው:: አንድ ጸሐፊ :-

"ከንግግርህ ይልቅ፥ ማንነትህ አጉልቶ ስለሚናገር፥ የምትናገረውን መስማት አልችልም።" እንዳለው ነው። (ራልፍ ዋልዶ ኢመርሰን)

* የድምፅ ሞገድና የመልዕክቱ ተቀባይ አቀባበልና አተረጓጎም የመልዕክቱን ንፅህና ሊያደበዝዘው ይችላል። ስለዚህ የወንጌል መልዕክት የምናስተላልፈው አገልጋዮችመልዕክቱን በጥራትና በብቃት፥ መልዕክት ተቀባዩ ሕዝብ ሊገባውና ሊቀበለው በሚችለው መንገድ ለቃሉና ለመንፈስ ቅዱስ በመገዛት በብዙ ጥንቃቄ ልናስተላልፈው ይገባል።

5. የሰዎች ምላሽ፥ ምክርና፥ ትችት መቀበል (FEEDBACK) :-

* የወንጌልን መልዕክት የሚያስተላልፈው ሰው መልዕክቱ በድምፅ ሞገድ፥ ወይንም በሰሚዎቹ አደማመጥና አተረጓጎም አለመቆራረጡንና ልባቸው ውስጥ መግባቱን፥ በትክክልም መረዳታቸውን በምን ያውቃል?!

የዚህ ጥያቄ መልስ ያለው መልዕክት የሚያስተላልፈው ሰው አብረውት ለሚያገለግሉትም ይሁን፥ የመልዕክቱ ተቀባይ ለሆነ ሕዝብ ምላሽ፥ ምክርና፥ ገንቢ ትችት ለመቀበል ባለው ክፍትነት ነው። የመልዕክቱ ተቀባይ ሕዝብ ሰሚና ተቀባይ ብቻ ከሚሆን ይልቅ፤ በሰማው ነገር ላይ በመነሳት የራሱን ምላሽ፥ ሃሳብ፥ ምክርና፥ ገንቢ ትችት በመስጠት በተራው መልዕክት አስተላላፊ መሆን ይጀምራል። በውስጡ ያለውም የመረዳት ደረጃ መገለፅ ይጀምራል። ይህ በተለይም የወንጌል ስርጭት በምናካሂድበት ጊዜ እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው። የሰዎች ምላሽ፥ ምክር፥ ሐሳብእና ገንቢ ትችት ቢያንስ ለአራት ምክኒያቶች ይጠቅማል።

5.1 የወንጌልን መልዕክት ለማስተላለፍ የምናደርገው መግባባት ከአንድ ሰው ብቻ ከሚሆን ይልቅ፤ ከሁለት ወገን የሚደረግ እንዲሆን ያደርገዋል። በዚህ ሂደት ውስጥ ግልፅነትና እውነተኝነት ባለው መንገድ ከመልዕክቱ ተቀባዮች ጋር ለመወያየት እጅግ ይረዳል። ስለዚህ የመልዕክቱ ተቀባዮችም በመግባባት ሂደት ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል። በዚህ የውይይት ሂደት ውስጥ ልቡን፥ አዕምሮውንና ፈቃዱን በመስጠት እንዲያስብና እንዲያውጠነጥን ያደርገዋል።

5.2 የሰዎች ምላሽ፥ ሐሳብ፥ ምክርና ገንቢ ትችት መቀበል መልዕክት የሚያስተላልፈው ሰው የወንጌሉን መልዕክት በጥራትና በብቃት፥ በግልፅነትና በእውነተኝነት፥ ለሕዝቡ ሊገባ በሚችል መንገድ ለማስተላለፍ እንዲችል በበለጠ ያዘጋጀዋል። እንደ ወንጌል አገልጋዮች ሁልጊዜ መጠየቅ ያለብን "የመልዕክቱ ተቀባይ ሕዝብ/ ሰው በመረዳት ሰምቷል ወይ? ወይንስ የድምፅ ሞገድ የመልዕክቱ ዋና ይዘት እንዳይ

ሰማ አግዶታል? የመልዕክቱ ንፅህና እንዲጭበረበር አድርጐታልን? የሰው ምላሽ የመልዕክቱ ተቀባይ ልናስተላልፈው የፈለግነውን የወንጌል መልዕክት በመረዳት እን ዲቀበለው ያደርገዋል። ምክኒያቱም የወንጌል አገልግሎት የሞትና የሕይወት ጉዳይ የሆነና ወሳኝ፤ መንፈስ ቅዱስም የሰውን ሕይወት የመለወጥ ኃይሉ የሚገልጥበት፥ አድማጩ ለዘለዓለም ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ውሳኔ የሚያደርግበት፥ የሰማይ መላዕክትም በአንክሮና በአድናቆት የሚጠባበቁበት የከበረ አገልግሎት ነው!!!

5.3 <u>የሰዎችን ምላሽ መቀበል የመልዕክቱ ተቀባይ የሆነው ሰው/ ሕዝብ ለመቀ በል ያለው ፍላጎት ምን ያህል መሆኑንና የት ደረጃ ላይ እንዳለም ያመለክተናል።</u> የመልዕክቱ ተቀባይ በክርስቶስ መስቀል ውስጥ የሚገኘውን መልስ ለማግኘት የሚያ ስችሉ ትክክለኛ ጥያቄ እንዲጠይቅ አድርጎታል ወይ? የበለጠ የመልዕክቱ ማብራሪ ያ ለምስማት ዝግጁ ነው ወይ? ክርስቶስን ለመከተል ተዘጋጅቷል? የሚሉት ጉዳዮች ለማጤን ይረዳል። የወንጌልን መልዕክት በትክክል ለማስተላለፍ የሚፈልግ ሰው ምንም ቢሆን ለሰዎች ምላሽ ቅድሚያ ይሰጣል።

5.4 <u>የመልዕክቱ ተቀባይ የሆነው ሕዝብ ምላሽ ለመስማት አለመፈለግ "የምትለ ው ነገር አይገደኝም፤ ብቻ እኔ ልናገር!" የሚል ያልተፈለገ መልዕክት ስለሚያስተላ ልፍ ለአገልግሎታችን እንቅፋት ይሆናል።</u> የወንጌልን መልዕክት የሚያስተላልፈው ሰው "የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር፥ የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነ ውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።" (2ጢሞ. 2፥ 15) የሚለው ቃል በሕ ይወቱ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ያደርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ የመልዕክቱ ተቀባ ይ የመረዳትና የግንዛቤ ደረጃውን የሚንቅና የሚሳደብ ያስመስለዋል። ስለዚህ የወን ጌል አገልጋዮች ሁሉ የሰዎችን ምላሽ ለመስማት ክፍትነት ሊኖራቸው ይገባል።

**ሐ. "ከሻነን - ዊቨር የመግባባት ሞዴል" የምንማረው:-**

- ምንጭ የነበረው ሰው የመልዕክቱ ተቀባይ ሆኖአል፤ የመልዕክቱ ተቀባይ የነበረ ው ደግሞ ምንጭ ሆኖአል። ስለዚህ እንደ አገልጋዮች በአንድ ጊዜ የመልዕክቱ ምንጭና ተቀባይ ነን ማለት ነው።
- መልዕክቱን በምናስተላልፍበት ጊዜ የመልዕክት ተቀባዮቹ ምላሽ፥ ምክር፥ ሐሳ ብና፥ ገንቢ ትችት ለመቀበል ራሳችንን በመስጠት፤ የዘራነውን ፍሬ የሰሚዎቹን የአቀባበል ደረጃና ሁኔታ በማስተዋል "በመንገድ ዳር፥ ... በጭንጫ ላይ፥ ... በእሾህ መካከል፥ ... ወይንም በመልካም መሬት" መውደቁን እናረጋግጣለን። (ማር. 4፥ 1-20) ልብ ብለን ካስተዋልን <u>ሦስት አራተኛው እጅ በክፉ የተያዘ</u>

ዓለም ነው:: ስለዚህም ብዙ ያምና ጸሎት፥ ፕላንና ዝግጅት፥ የሚጠይቅ ከመሆ ኑም በላይ፤ የምንሰብከው የማይለወጠው ወንጌል ሕዝብ ሊገባው በሚችል መንገ ድና በጥንቃቄ ወቅታዊ በሆነም መልክ ልናቀርበው ይገባል::

- እውነተኛ መግባባት ተካሂዷል ማለት የሚቻለው የመልዕክቱ ምንጭ፥ መልዕክ ቱ የሚተላለፍበት መንገድ፥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት፥ የድምፅ ሞገድ፥ የመልዕክቱ ተቀባይ፥ እና የመልዕክቱ ተቀባይ ምላሽ ሲኖር ብቻ ነው!!!
- የወንጌል መልዕክት በምናስተላልፍበት ጊዜ የመጨረሻው ዓላማችን ሰዎች በግላ ቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማግኘት መቻላቸውና በእግዚአብሔር ቤት መተከላቸው ነው!!!

## IV. የመግባባት ሞዴሎች:-

### ሀ. በመልዕክቱ ምንጭ ላይ ያተኮረ አቅርቦት:-

መግባባት በባሕርዩ እያደገ መምጣት የሚችል ችሎታ ነው:: ለአንዳንዶች ከሌ ሎች የበለጠ ሊቀላቸው ይችላል:: አንዳንዶቻችን በተፈጥሮ የተሰጠን ስብዕና መግባ ባትን የሚወድ ሲሆን፤ ሌሎቻችን ደግሞ የተሰጠን ስብዕና ስብስብ ያልና በቀላሉ ራሱን የማይገልጥ ሊሆን ይችላል:: አንዳንዶቻችን ከሰው ጋር በቀላሉ መግባባት የምንችል ስንሆን፤ ሌሎቻችን ደግሞ አስበን ካልሆነ በስተቀር በቀላሉ ወደ ሰው መቅረብ የሚያዳግተን ልንሆን እንችላለን:: ምንም ዓይነት ስብዕና ቢኖረንም መግባ ባት በምንጀምርበት ጊዜ በመልዕክቱ ምንጭ ላይ ያተኮረ አቀራረብ ነው::

**1. በራስ ላይ ያተኮረ የመግባባት አቅርቦት:-**

እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ ወይ ልምምድ ከማጣት፥ ሰውን ከመፍራት፥ መልዕክ ቱን ለማቅረብ ሳይቀለን ሲቀር፥ ወይንም መልዕክቱ በጥራትና በጥልቀት ሳይገባን ሲቀር የሚደረግ የመግባባት አቅርቦት ነው::

2. እንዲህ ዓይነት አቀራረብ የሚመጣው የመልዕክት አቅራቢው ከሚገባ በላይ ከሚያስተላልፈው መልዕክት ይልቅ፤ ስለ ራሱ ብዙ ማሰብ በሚጀምርበት ጊዜና፥ በራሱ ሲዋጥ ነው:: የመልዕክቱ ተቀባይ የሆነው ሕዝብ የሚታዘበውና የሚተቸው ሲመስለው፥ በራሱ ዓይንም ሆነ በሌሎች ሰዎች ዓይን ተቀባይነት የሚያጣ ሲመስለ ው ራሱን በማሰብ ይዋጣል:: በዚህ ሲፈተን አለባበሱ፥ የአነጋገር ስልቱ፥ በፊቱና በአቋቋሙ የሚገልፃቸው የስሜት ሽግግሮች ሁሉ ሊለዋወጥ ይጀምራል::

3. የወንጌልን መልዕክት የሚያቀርበው ሰው ሰሚዎቹ አይቀበሉኝም ከሚል፥ ወይም ከአገልግሎት ልምምድ ማነስ፥ የቃሉ ባለቤት በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይ

ል ለመደገፍ ካለመቻል፥ የሚሰሙኝ ሰዎች ስለ እኔ ምን ያስባሉ? ከሚል ፍርሃት የተነሣ በራሱ ወጥመድ ውስጥ ሊያዝ ይችላል። ስለዚህ የሚያዋጣው በጸሎት ራሱን ና ሕዝቡን አሳልፎ በመስጠት፥ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በመደገፍና በእምነት መቆም ብቻ ነው!!!

4. ራስ ተኮር የሆነ አገልግሎት የሚፈለገውን ፍሬ ማምጣት አይችልም። ይህ የስሜት ሽግግር የመልዕክቱ ንፅህና እንዲመቻምችና ግልፅነትን፥ ቅንነትና፥ እውነተ ኝነትን እንዲያጣ ያደርገዋል። ከዚህም ሌላ የሰዎች ምላሽ በሚመጣበት ጊዜ መልዕ ክት አቅራቢውን ከሚያንፀውና ለበለጠ ዝግጅትና እድገት ከሚያሸጋግረው ይልቅ፣ ይሰብረዋል፥ ተስፋም ያስቆርጠዋል።

- አንደኛ ራስ ተኮር የሆነ አገልግሎት በአገልጋዮች ሁሉ የሚያልፍ በመጀመሪያ የአገልግሎት ዘመን የሚመጣ ልምምድ ቢሆንም፣ በዚሁ ግን መቀጠል የለብን ም። በመሠረቱ አግልግሎት የእኛ ጉዳይ አይደለም፣ የጌታ ጉዳይ እንጂ!!! ( IT IS ALL ABOUT HIM!!!)
- ***መልዕክቱም መልዕክተኛውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው!!! መልዕክታችን ይሁን፥ የመልዕክታችን ይዘት፥ የሰውን ልብ መንካት የሚችለውና፥ በሕዝብ መካከል የከበረ የማዳን ሥራውን የሚሠራው፥ ሰውንም የሚለውጠው፥ እርሱ ነው!!!***
- ሁለተኛ አስፈላጊ የሆነ የአገልግሎት ሥልጠና መውሰድና በወንጌል አገልግሎት የቆዩ ነባር የሆኑ አገልጋዮች ማማከር፥ ለወንጌል አገልግሎት የሚረዱንን መጣ ጥፎች፥ ስለ አመራር የተጻፉ በስለት ያላቸው መጻሕፍትና፥በደቀ መዝሙርነት ላይ የተጠኑ ጽሁፎች በየጊዜው ማንበብ ከራሳችን ወጥመድ ለመውጣት ይረዱ ናል።
- ሦስተኛ እግዚአብሔር እኛን ለመጠቀም እንደሚወድና እንደሚችል፣ ሆኖም ሊቀርፀን፥ ሊለውጠንና፥ ሊያሳድገንም እንደሚፈልግ፣ እድገታችንንም እርግጠ ኛና ጽኑ ለማድረግ የተለያዩ መንገዶችንና ሁኔታዎችን እንደሚጠቀም፣ ለዚህም ክቡር ሥራው በመታዘዝ ራሳችንን በፊቱ መቀደስ በጣም ወሳኝ ነው።

## ለ. በመልዕክቱ ላይ ያተኰረ አቅርቦት፡-

1. አሁን ራስ ተኰር ከሆነ አገልግሎት ወጥተን በመልዕክቱ ላይ የሚያተኩር አገልግሎት መስጠት ስለምንጀምር ደስ ይበለን! የልባችን ትርታ በኃይል ከመምታት አቁሟል፣ ስለ ራሳችን ብዙ ከማሰብና ከመጨነቅ ወጥተናል፣ ከዚህ የላቀ የወንጌል መልዕክት ላይ በሙሉ ልብ ማሰብ ጀምረናል።

2. በመልዕክት ላይ ያተኰረ አገልግሎት የሚሰጥ አገልጋይ "ለማቀርበው የወንጌል መልዕክት ፍትህ በማድረግ ላይ ነኝ ወይ? የመልዕክቱ ጸሐፊ ሊሰጠው የፈለገውን ትርጉም በመረዳትና፥ የጻፈላቸው ሰዎችም በዚያ ዘመን የተረዱት መረዳትና የሰጡት ትርጉም በማስተዋል አቅርቤአለሁ ወይ? የወንጌልን መልዕክት ንፅህና ለመጠበቅ ምን ያህል ጥንቃቄ አድርጌአለሁ? ወይንስ ደግሞ የመሰለኝ የራሴ አስቀድሞ የተጠነሰሰ ሐሳብ ይዤ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አንብቤለታለሁ ወይ? በዚህ ደረጃ ዋናው ትኩረት የመልዕክቱ አቅራቢ፥ ወይም ተቀባይ መሆኑ ቀርቶ፣ በመልዕክቱ ላይ ያነጣጠረ ነው።

3. የመልዕክት አቅራቢው ሕዝቡን ለመድረስ ሲል በራሱ ስሜት ላይ ከማተኰር ወጥቶ በመልዕክቱ ተቀባይ ሕዝብ ላይ ሕይወቱን ለማፍሰስ እንዴት ይችላል? ለዚህ መልስ የመልዕክቱ ይዘት ሰው አጥንትና ልብ ውስጥ እንዲገባ በመፍቀድና የራሱን ስሜት በሁለተኛ ደረጃ በመያዝ መቆጣጠር ሲችል ነው። በዚህ ጊዜ ነው የመግባባት ደረጃ እየደመቀና እየሠመረ የሚሄደው።

## ሐ. ሌላነት ላይ ያተኰረ አቅርቦት፡-

1. የወንጌል አገልጋዮች "ደርሼበታለሁ፥ አውቄዋለሁ" ማለት ሲጀምሩ በውስጣቸው ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ መሳሳትና መቀጨጭ የጀምራል። የራሳቸውን "ራስ ተኰርነት" ለመቆጣጠር መቻላቸውና፥ የመልዕክቱንም ይዘት መረዳታቸው የመጨረሻው ዳርቻ የደረሱ ይመስላቸዋል። እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ግን አሳዛኝ ነው። ወንጌልን በመግባባት ማስተላለፍ፥ መልዕክቱንም መናገር መቻል ብቻ አይደለም።

2. የመልዕክቱን ይዘት የመልዕክቱ ተቀባዮች በሙሉ መረዳት መቀበላቸውን እርግጠኛ መሆንን ይጠይቃል። የወንጌል ሥርጭት ዋና ዓላማው የሚሰማው ሰው በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ለክርስቶስ ለማድረግ እንዲችል ነው። ይህ የከበረ ውሳኔ ግን በድምፅ ሞገድ (ባህላዊ፥ ሥነ መለኰታዊ፥ ግላዊ፥ ወይንም መንፈሳዊ) ሊታገድ፥ ሊቆራረጥ፥ ወይም ሊጭበረበር ይችላል። በራሱና በመልዕክቱ የተዋጠ

አገልጋይ እነዚህ ተግዳሮቶች እንዳሉ አውቆ በጸሎት ለመትጋትም ይሁን፥ በሰው ልብ ውስጥ ያሉትን አጥሮች ለመስበር የሚያስችል ልዩ ጸሎትም ይሁን ፕላንና ዝግጅት አያደርግ ም።

3. የወንጌል አገልጋዮች "እኔ ራሴው ነኝ፤ ብቃት አለኝ" ማለት ሲጀምሩና ራሳ ቸውን የነገሩ አዋቂዎች አድርገው በሚያስቡበት ጊዜ ያለ ምንም የጸሎት ትጋትና ድጋፍ መድረክ ላይ ራሳቸውን ማውጣት ይጀምራሉ። በራሳቸው እውቀትና ልምም ድ ላይም ይደገፋሉ። እንዲህ ዓይነት አገልጋዮች የጠራቸው፥ የለያቸውና፥ የቀባቸ ውን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል፤ የተጠሩለትንም የወንጌል መልዕክትና የተጠሩለትን ም ሕዝብ መናቅና መርገጥ ይጀምራሉ። የራሳቸው ድካምና ጉስቁልና አይታያቸው ም። የመልዕክቱ ተቀባይ ሕዝብ ምላሽ፥ ምክር፥ ሐሳብ፥ ወይም ገንቢ ትችት ሲሰጣቸውም ለመስማት ቅንነት ያጣሉ።

4. የወንጌል አገልጋዮች ሌላነት ላይ ያተኰረ አገልግሎት በየጊዜው ልናሳድገ ው፥ ማድረጋችንም ልናረጋግጥ ይገባናል። ቀጣይነት፥ ዘላቂነትና፥ ያልተበጣጠሰ የወንጌል አገልግሎት ይኑረን ካልን፤ ሌላነት ላይ ያተኰረ አገልግሎት ማሳደግ ይኖርብናል።

## V. የመግባባት ችሎታን ማሳደግ:-

### ሀ. ዐውድ:- (CONTEXT)

❖ የወንጌል አገልጋይ ያለበት ዐውድ መሪው ከመልዕክት ተቀባዩ ሕዝብ ጋር አብሮ እንዲነዝር ያደገዋል።

1. <u>ከመናገር በፊት መስማት</u>:- (ምሳሌ 18፥ 13፤ ያዕቆብ 1፥ 19-20) የወንጌል አገልጋይ ራሱ እንዲሰማ ከፈለገ፥ በመጀመሪያ መስማት መቻል አለበት። የመልዕክቱ ተቀባይ ሕዝብ ያለበትን ዐውድ በጥንቃቄ ማጤን፥ መረዳት፥ ልቡ የሚያሳምመውን ማወቅና፥ መስማት አገልግሎቱን የሠመረ ያደርገዋል።

2. <u>የሰውን አፈጣጠር መረዳት</u>:- (ምሳሌ 12፥ 18)

ከአንደበት የሚወጣው ቃል ኃይልኛ ነው፤ ወይ ሊያንፅና ሊያሳድግ፥ ወይንም ደግሞ ሊያፈርስና ሊያቀጭጭ ይችላል። ለዚህም ከወንጌል አገልጋይ የበለጠ ብዙ ጥንቃቄ ማድረግ ያለበት ያለ አይመስለኝም። ሐዋርያው ጳውሎስ ያለው ቃል እውነ ትኛ ነው፤ እንዲህ የሚል:- "ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ ይህንም አዘውትር። ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፤ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ ራስ ህንም የሚሰሙህንም ተድናለህና።" (1ጢሞ. 4፥ 15-16) በሌላ ሥፍራም:- "ስለዚህ

እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፥ ነፋስን እንደሚጐስም ሁሉ እን ዲሁ አልጋደልም፤ ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጐሰምኩ አስገዛዋለሁ።" ይላል። (1ቆሮ. 9፥ 26-27)

የወንጌል አገልጋይ የሆነ ሰው ሰዎች እርግጠኝነት የሌላቸውና የሚዋልሉ፥ የስብዕናቸው ክብር ፈላጊ፥ የወደፊት ተስፋ እንዲኖራቸው የሚፈልጉና በግለኝነት የተሞሉ መሆናቸውን ልንገነዘብ ይገባል።

3. <u>የስሜት ንቁነትና የመረዳት ችሎታ መያዝ</u>፦ (ምሳሌ 25፥ 20)

የወንጌል አገልጋዮች ዐውዱን በመረዳትና በመልዕክቱ ተቀባዮች ዘንድ ያለውን የስሜት ለውጥ፥ ወይም ሽግግር ማስተዋልና መረዳት መቻል በጣም ወሳኝ ነው። በፊታቸው የሚታየውን ሁኔታ ማየትና መረዳት አስፈላጊ ነው። ይኼ የአቀባበላቸ ውን ደረጃ ያሳየናል።

**ለ. አቅርቦት፦**

❖ *የምናቀርብበት አቀራረብ ማሰብ መሪውን የሚጠቀምባቸውን ቃላት፥ ሐሳቦች፥ ዐረፍተ ነገሮች፥ የአገላለፅ ቋንቋ አስተውሎ እንዲመርጥ ያደርገዋል።*

1. <u>በለዘበና ጸጋ በሞላበት ቃል መናገር</u>፦ (ምሳሌ 15፥ 1)

የራሳችንን ስሜት መቆጣጠር ስንችልና መልዕክቱንም ስንረዳ ግማሽ ደረጃ ላይ ደርሰናል። ከዚያ በኋላ ግን የመልዕክት ተቀባይ ሕዝብን በማሰብ በለዘበና ጸጋ በተ ሞላበት ቋንቋ መናገር መቻል አለብን። ሐዋርያው ጳውሎስ "*ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ እንደሚያስፈልግ ለማነፅ የሚጠቅም ማናቸውም በጐ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይወጣ።*" ይላል። (ኤፌ. 4፡29)

2. <u>ሐቀኛ/ እውነተኛ መሆንና በቅንነት መናገር</u>፦

የወንጌል አገልጋዮች የመልዕክቱ ተቀባይ ሕዝብን ለመጫንና ለመግዛት ከመሞ ከር ፈፅሞ ልንታገድ ይገባል። በማቆላመጥ፥ በማታለል፥ አጉል የሆነ "የብልጽግና ወንጌል" ተስፋ በመስጠት፥ በፈጠራ፥ በውሸት፥ ወይንም የራሳችንን ጥቅም በመፈለ ግና ሕዝቡንም የእርከን መወጣጫ ለማድረግ ከመፈለግ የወንጌልን አገልግሎት ልና ካሂድ አይገባም። ከዚህ ይልቅ በሐቀኝነት፥ በእውነትና በቅንነት፥ በፍፁም ፍቅርና ትሕትና የተሰጠንን የወንጌል አደራ ልናስተላልፍ ይገባል።

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## አመራርና ችግሮችን መፍታት

- *“የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው እንደሆነ÷ በእርሱና በጠላቶቹ መካከል ስንኳ ሰላምን ያደርጋል፡፡” (ምሳሌ 16:7)*
- *“<u>ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል</u> ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፡፡ ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ÷ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው÷ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተፅፎአልና፡፡...ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ፡፡” (ሮሜ 12:18-21)*
- *“ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ፡፡ መራርነትና ንዴት÷ ቁጣም÷ ጩኸትም÷ መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንት ዘንድ ይወገድ፡፡ እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሮኆች ሁኑ÷ <u>እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ ፡፡ (ኤፌ. 4:29-32)</u>*
- *<u>በአንድ ልብ</u> ሆናችሁ <u>በአንድ አፍ</u> እግዚአብሔርን እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት ታከብሩ ዘንድ የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስ በርሳችሁ <u>በአንድ አሳብ</u> መሆንን ይስጣችሁ፡፡” (ሮሜ 15:5-6)*

### I. መግቢያ:-

በቤተ ክርስቲያን አመራር የሚያገለግሉ መሪዎች ሰው ከመሆናቸው የተነሳ በመካከላቸው ችግሮችና አለመግባባቶች መፈጠራቸው ልንክደው የማንችለው እውነት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ መሪዎችም ከሚያገለግሉአቸው ሰዎች÷ ወይንም ጉባዔ ጋር ውጥረትና ጭንቅንቆሽ መታየት ከጀመረም ቆይቷል፡፡ የችግሩ ዓይነቶች መልክ ብዙና ዘርፈ ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ፤ አንዳንዴ የነገሩ ውል የት እንዳለ ለማወቅ በቅጡየማይታወቅበት ጊዜ ቀላል አይደለም፡፡

በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከልም ይሁን በመሪዎችና በምዕመን መካከል ችግሮች ሲነሡ እንዴት እንደምንይዛቸውና እንደምንፈታቸው ማወቅ ወደ የበለጠ ግንኙነታችን እየሠመረና እየደመቀ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡ ወይንም ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱን ምሥክርነት የሚያስጠፋ፥ ለምዕመኑ መከፋፈል ምክኒያት የሚሆንና ቤተ ክርስቲያኒቱን ጥሎ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄድ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተጨማሪም በውጭ ላሉትም ለማያምኑ ሰዎችም ማሰናከያ ሊሆን ይችላል፡፡ አገል ጋዮችና መሪዎች በአንድ ላይ በሚያገለግሉበት ጊዜ የተለያየ አመለካከት በመሃላቸ ው መከሰቱ ብርቅ ነገር ሊሆን አይገባም፡፡ ነገር ግን ይህ ወደ ክርክር፥ መጠላላትና ፥ መገፋፋት ይለወጥና እጅግ የሚያሳስብ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ችግሮች በመካከ ላችን ሲነሡ፥ ወይ ምንም እንደሌለ ማሰብ እንችላለን፤ ወይም በነገሩ ማጉረምረም እንችላለን፤ ወይንም አንድን ሰው መውቀስ እንችላለን፤ ወይም በሰሚ ሰሚ በወሬ ላይ ተመርኩዘን ልንፈታው ልንሞክር እንችላለን፡፡ መፍትሔው ግን የችግሩ ዓይነት መነሻና ምክኒያት እንደሚገባ ከሚመለከታቸው ሰዎች ሁሉ ጋር በመገናኘትና በመ ወያየት ችግሮቹን ለመፍታት መቻል ነው፡፡ የችግሮቹ መከሰት የሚካድ ባይሆንም፥ እንዴት ግን ልንፈታቸው ይገባል? የሚለው ጥያቄ በእርጋታ ልንመልሰው የሚገባ ን ነው! የህመም ምልክቶች ለማከም ከመሞከር ይልቅ፥ ዋናውን ቁስል ፈልጎ ማግኘ ትና፥ ቢያሳምምም ቁስሉን አጥርቶ ማከም ይበልጣ ል፡፡ አሁንም ልንጠነቀቅ የሚገ ባን በትንንሽ ጉዳዮችና ይኸን ያክል የሞትና የሕይወት ጉዳይ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ጊዜያችንን እንዳናጠፋ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ችግሮችበመደረግ የሚጠፉ ናቸው፡፡ ከዚህ ይልቅ የሞትና የሕይወት በሆኑ ዋና ጉዳዮችና የቤተ ክርስቲያኒቱን ደህንነት በሚገዳደሩ ጉዳዮች ላይ ልናተኩር ይገባል፡፡

## II. መሪዎች ልንመልሳቸው የሚገቡን ጥያቄዎች፡-

- በዚህ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔርን እንዴት ደስ ላሰኘውና ላስከብረው እችላለሁ?
- የተነሳውን ችግር እንዴት አድርጌ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ኃይል ለመግለጽ ምክኒያት እንዲሆን የተሰጠኝ ዕዳሎት እንደሆነ ላደርገው እችላልሁ?
- መቼ ነው ችግሩን እያየሁ እንዳላየሁ በልበ ሰፊነት ልይዘው የሚገባኝ? ዳርቻው ስ እስከምን ድረስ ነው?

- በየጊዜው ለችግሮች መነሳት ምክኒያት የሚሆነውን የራሴን ልማድና ዝንባሌ÷ ባሕርይ መለወጥ እንዴት እችላለሁ?
- የሠራኋቸውን ስህተቶች ወይም በደል÷ በበደልኳቸው ሰዎች ፊት እንዴት መና ዘዝና ይቅርታ መጠየቅ እችላልሁ?
- የራሴን መብት ማስጠበቅ የምችለውና የማስረግጠው መቼ ነው?
- ሌሎች መሪዎች ወይም ከምዕመን መካከል የተሳሳቱት ወይም የበደሉትን በድል እንዴት ማረም ይኖርብኛል?
- የበደሉኝን ሰዎች ይቅር ማለትና ከእነርሱም ጋር ለመታረቅ እንዴት እችላልሁ?
- በይቅርታና በእርቅ መካከል ያለው ግንኙነትና ልዩነት ምንድር ነው?
- መቼ ነው የበደለኝን ሰው "ይቅር ብያለሁ" ማለት የምችለው?
- ፍትሕ የተሞላውና ለአዕምሮ የሚመች ስምምነት እንዴት ማድረግ ይቻላል?
- ቤተ ክርስቲያን በመሃላችን ጣልቃ እንድትገባ መቼ መጠየቅ ይኖርብኛል?
- ለአዕምሮ የማይመቹና ይቅርታ ለመቀበልም ይሁን ለመስጠት የማይፈልጉ ሰዎ ች ሲያጋጥሙኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?
- ለክርስቲያን ወደ ፍርድ ቤት መሄድ መቼ ነው የሚችለው? ወይንስ በ1ቆሮንቶስ 6:1-6 መሠረት አይችልም ወይ?

## III. ይቅርታና ምሕረት :-

- 1. "*<u>ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል</u> ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።*" (ሮሜ 12:18-21) ሐዋርያው ጳውሎስ በሰጠው መልዕክት ሁለት መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች አመልክ ቷል። አንደኛው:-"*ቢቻላችሁስ*" የሚለው ሆኖ፤ ሁለተኛው ደግሞ "*በእናንተ በኩል*" የሚለው ሐሳብ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ "ቢቻላችሁስ" የሚለው ቃል የተጠቀመ ው የማይቻልበትም ጊዜ አለ ማለት ነው። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 15:1-29 ላይ በአንድ ወገን እርሱና በርናባስ÷ በሌላ ወገን ደግሞ የሐሰት አስተማሪዎች የነበሩት የአይሁድ አስተማሪዎች መካከል መለያየት በተፈጠረበት ጊዜ ከእነርሱ ጋር የሚያስ ማማና የሚያደራድር ነገር እንዳልነበረው አይቷል። ከዚህም ሌላ በእርሱና በበርናባ ስ መካከል አለመግባባት በተፈጠረበትም ጊዜ በመልካም መንፈስና ዓላማ ቢሆንም÷ አብረው መጓዝ ያልቻሉበት ጊዜም ነበር። <u>ሐዋርያው ጳውሎስ "በእናንተ በኩል" በሚልበትም ጊዜ ሌላውን ሰው ለመለወጥ÷ ለመቆጣጠርና÷ ለማስተካከል አቅሙ</u>

እንደሌለንና፥ መብትና ግዴታችን ራሳችንን በጌታ ፊት መለውጥ እንደሆነ ለመግለ ጽ ፈልጎ ነው።

❖ 2. "*የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና።*" (ማቴ. 5:7)

"ጸጋ" በኃጢአትና በሀሊና ወቀሳ ላይ ይጫማል። "ምሕረት" ደግሞ በኃጢኤት ሰበ ብ ላይ፥ ማለትም በሥቃይ፥ በመከራ፥ በውርደትና በመንፈሳዊ እራቁትነት ላይ ያተኩራል።

- *ምሕረት ማሳየትን ሌላው ሰው ቢሸሽም፥ እጅን መዘርጋት ነው!*
- *ሌላው ሰው ታማኝ ባይሆን፥ ከልባችን እርሱን ማመን ነው!*
- *ሌላው ሰው ስጦታችንን ቢያናንቅና ለመቀበል ባይፈልግም፥ ለእርሱ ስጦታን ለመስጠት መጓጓትና ማድረግ ነው!*

❖ 3. "የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።" (ማቴ. 5: 9) የልብ ንፅህና ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው ከሌላው ሰው ጋር ሰላምን ለመ ፍጠር የሚፈልጉ። ከሰው ጋር ሰላም መፍጠር ለማድረግ ያህል፥ እርሱ ደስ እን ዲለው አይደለም። የእግዚአብሔር ሰላም ምንም ዓይነት ዋጋይከፈል፥ እውነትን አመቻምቾን የሚደረግ አይደለም። ሰላምን ማድረግ ርካሽ ጸጋ አይደለም። ስለ ዚህ የሕይወትም ይሁን የዶክትሪን ንጽሕና የሌለው የቤተ ክርስቲያን አንድነት ለመፍጠር ከክርስቶስ መብትም ሆነ ጥሪም (MANDATE) አልተሰጠንም!!!

❖ 4. ይቅርታ ማድረግ የአንድ ደቂቃ ጉዳይ ነው፤ እርቅ ግን ጊዜ ሊወስድ ይችላል። የበደለው ሰው ያበላሸውንና የሰበረውን መታመን እንደገና መልሶ ማ ግኘት አለበት። ስለዚህ አንድ የበደለንን ሰው "ይቅር ብየዋለሁ፥ ከእርሱም ጋር ታርቄአለሁ" ማለትየምንችለው ከዚህ በፊት በድሎን እንደማያውቅና ከመጣላ ታችን በፊት ወደ ነበረውነባራዊ ነፃነት ሊመለስ ሁኔታ ስናመቻችለትና ነፃነቱን ስናውጅለት ነው!!!

❖ 5. ይቅርታና ምሕረት ማድረግ የበደልንን ሰው በቅንነት ማሰብን ይጠይቃል።

- *በበደለን ሰው ስሜት ውስጥ መግባትን፤*
- *በጫማው ውስጥ እግራችንን ማስገባትን፤*
- *በተቻለን መጠን ለምን እንዳደረገው፥ ወይም እንደተናገረው በጥልቀት ለመረዳት ልባዊ ጥረት ማድረግን፤ ይጠይቃል!*

❖ ለጌታ ኢየሱስ በመገዛት በሕይወታችን የተፈፀመ መልካም ድርጊት፥ ይቅር ታና ምህረትን ለመለማመድ የሚጎረብጥ፥ የሚያሳምምና የሚያቆስል፥ የበ ደለንን ሰው ድርጊቶች መዋጥ መቻልን ይጠይቃል።

❖ የበደለንን ሰው እንደ ገና መልሰን እንዴት ገንዘባችን እንደምናደርገው ወደ መልካም መንፈሳዊ ህብረትና የግንኙነት ሥምረት እንደምንመልሰው ማሰ ብና ለራሳችን የማይመቹ ከባድና ጠንካራ ውሳኔዎችን መወሰን ይጠይቃል

❖ 6. አብሮ በሰላም ለመኖር፥ ይቅርታና ምህረትን ለማድረግ እየፈለግንም የበደለን ሰው ግን ሳይፈልግ ሲቀር ምን እናደርጋለን?

➢አንደኛ "ሰውነታችንን እግዚአብሔርን ድስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስ ም መስዋዕት አድርገን ማቅረብና በልባችን መታደስ ፈቃዱን መለየትና ማድ ረግ" ይኖርብናል። (ሮሜ 12፡ 1-2)

➢ሁለተኛ "እግዚአብሔር ለእኛ እንደ ሰጠን የእምነት መጠን እንደ ባለ አዕምሮ ማሰብ፣ ወይ ከሚገባ በላይ ራሳችንን ሳንለጥጥ፥ ወይንም ራሳችን ን በማናናቅና በማጣጣል እንዳንመለከት" ያስፈልጋል። (ሮሜ 12፥ 3)

➢ሦስተኛ "እርስ በርሳችን ልንዋደድና" በተሰጠንም የፀጋ ስጦታ ልናገ ለግል "እርስ በርሳችን በመከባበር" እና "በአንድ አሳብ በመስማማት" ልንኖር ተጠርተናል። (ሮሜ 12፥ 4-13፥ 15-16)

➢አራተኛ "የሚያሳድዱንን ለመባረክና" "የሚረግሙንንም ለመመረቅ፣ የሚጠሉንን ለመውደድ" ተጠርተናል። (ሮሜ 12፥ 14፥ 17-21)

❖ 7. እንደ ክርስቲያን ስለ ክፉ (EVIL) ያለን እይታ፡-

✓አንደኛ ክፉ ልንጠላው ይገባል። (ሮሜ 12፥ 9)

✓ሁለተኛ ብድራትን ለመመለስ ግን አልተፈቀደልንም። (ሮሜ 12፥ 1 7፥ 19)

✓ሦስተኛ እንዲያውም የተጠራነው ክፉውን በመልካም እንድናሸንፍ ነው። (ሮሜ 12፥ 14፥ 20-21)

✓አራተኛ ክፉ መቀጣት አለበት፣ ነገር ግን ይህን ማድረግ የእግዚአብ ሔር እንጂ፥ የእኛ ኃላፊነት አይደለም። (ሮሜ 12፥ 17-19)

## IV. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናያቸው ግጭቶች:-

### ሀ. የብሉይ ኪዳን ዘመን:-

- አዳም የራሱን ኃጢአት ከመቀበል ይልቅ፥ ሔዋንን የማምለጫ ፍየል አድርጎ መውሰዱ:: (ዘፍ. 3፥ 1-21)
- አብርሃም መውሰድ የሌለበትን ሎጥን በመውሰዱ ምክኒያት (ዘፍ. 12፥ 1) በመካከላቸው በተነሳው አለመግባባት መለያየታቸው:: (ዘፍ. 13፥ 1-18)
- ይስሃቅ የእርሱን መኖር በሚጠሉ ሰዎች በተደጋጋሚ የደረሰበት መገፋት:: (ዘፍ. 26፥ 12-33)
- ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ጋር በመጣላቱና፥ ኤሳውም በእርሱ ላይ የነበረው መራራ መንፈስና የዘመናት ቁርሾ:: (ዘፍ. 25፥ 22-34፤ 27፥ 1-46፤ 33፥ 1-17፤ ትንቢተ አብድዩ 1፥ 1-21)
- ዮሴፍ በአሥሩ ወንድሞቹ ቅንዓትና ጥላቻ ምክኒያት ከቤት መውጣት፥ በጉድጓድ መጣል፥ ለባርነት መሸጥ፥ በእሥር ቤት መጣልና የአሥራ ሦስት ዓመታት መከራ መቀበል:: (ዘፍ. 37-50)
- የእስራኤል ሕዝብ መሪያቸው በነበረው በሙሴ ላይ ማጉረምረም፥ መንፈሱን ማሳዘንና፥ እርሱን ለመምታትም መጋበዝ:: (ኦሪት ዘኁልቅ)
- የሙሴ ወንድምና እህት የነበሩት አሮንና ማርያም በሙሴ አመራር፥ ይልቁንም በነቢይነት አገልግሎቱ ማጉረምረም:: (ዘኁ. 12፥ 1-15)
- ንጉሥ ሳኦል በንጉሥ ዳዊት ላይ ያሳየው ከፍተኛ የስሜት ሽግግር:- ከመውደድ ---- ወደ ጥላቻ ----- ወደ ግድያ ፕላን ------ ወደ ማሳደድ:: (1ሳሙ. 18፥ 9፥ 12፥ 15፥ 17፥ 29፤ 19፥ 1፤ 22፥ 17)
- የእስራኤል ንጉሥ የነበረው አክአብ በነቢዩ ሚክያስ ላይ ያሳየው ጥላቻ:: (1ነገ. 22፥ 8)
- የእግዚአብሔር ቤት ጠላቶች ከነበሩት ከጦቢያ፥ ሰንባላጥ፥ እና ጌሳም በነኅምያ ላይ የሥጋ ግድያ ሙከራ፥ የስም ማጥፋት ዘመቻና፥ የሐሰት ትንቢት:: (ነህምያ 2፥ 10፥ 19፤ 4፥ 3፥ 7-8፤ 6፥ 1-14)

### ለ. የአዲስ ኪዳን ዘመን:-

- በጌታ ደቀ መዛሙርት መካከል በየጊዜው ይታይ የነበረው የውድድርና የፉክክ ር መንፈስ። (ማቴ. 20÷ 20-28)
- በመጀመሪያይቱ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተነሳው የዘርና የባሕል ግጭት (የሐዋ. ሥራ 6÷ 1-7)
- በአንድ በኩል ሐዋርያው ጳውሎስና በርናባስ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የይሁዳ የሐሰ ት አስተማሪዎች (JUDAIZERS) መካከል የተነሳው የዶክትሪን ግጭት። (የሐዋ. ሥራ 15÷ 1-35)
- በሐዋርያው ጳውሎስና በበርናባስ መካከል የተሳው ግጭት። (የሐዋ. ሥራ 15÷ 36-41)
- በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መካከል ይታይ የነበረው ሥጋዊ መጠላላትና የባለ ንብረትነት ስሜት። (1ቆሮ. 1÷ 11-17፣ 3÷ 1-4)
- ሐዋርያው ጳውሎስ በግል የሚያውቃቸው በነበሩት አገልጋዮች በኤዎድያንና በስንጤኪያን መካከል ተነስቶ የነበረው ግጭት። (ፊል. 4÷ 2-3)

## V. ግጭቶችን የመፍታት እርምጃዎች:-

### ሀ. ግጭት እንዳለ መቀበል:-

በቤተ ክርስቲያን አሠራርም ይሁን፥ በሰው ግንኙነት መካከል የሚጋጩ ሐሳቦ ችና አመለካከቶች መኖራቸው ለግንኙነት ሥምረት እድገት በጣም አስፈላጊ ነው።

### ለ. የራስን ድካም መቀበል:-

ምንም ያህል ክርስቲያኖችና መሪዎች ብንሆንም፥ እያንዳንዳችን ሰው ከመሆና ችን የተነሳ የራሳችን ሥጋዊ ኩተት ካለፍንባቸው ልምምዶች ይዘን መምጣታችን የማንክደው ሐቅ ነው። ስለዚህ ከሰው አጠባበቃችን እውነተኝነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

1. ያለፍንባቸው ፍርሃቶች፥ ጉዳቶች፥ ወይንም የግል ቁስሎች አሁን ባለንበት ሁኔታ ላይ ተፅዕኖ ሊያመጣ ስለሚችል የራሳችን ውስጣዊ የስሜት ሂደት መገንዘባ

ችን በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲህ ማድረጋችን ራሳችንን ለመረዳት ከማገዙም በላይ ፥ ሌላውን ሰው በራሳችን መነፅር ብቻ እንዳንፈርድበት ይረዳናል።

2. በሌላ ሰው ላይ መነጫነጭ፥ ፈራጅ በሆነ መንፈስ፥ ወይንም በቁጣ መቅረብ ስንጀምር፥ የራሳችንን መንፈስ አስቀድመን መመርመርና፥ ካለፍንባቸው ሁኔታዎ ች ይዘነው የመጣነው ሥጋዊ ኮተት ካለ ማየት ይኖርብናል።

## ሐ. ግጭት የማሸነፍና የመሸነፍ ጉዳይ አይደለም፡-

አንዳንድ ሰዎች ከባሕርያቸው ብሉሽነት የተንሣ ከሰዎች ጋር ያላቸውን ግጭት ለመፍታት በሚወያዩበት ጊዜ አቀራረባቸው "ማሸነፍና መሸነፍ" (WIN-LOSE) በሚል ደረቅ አካሄድ ነው። ከዚህ ሁኔታቸው የተነሳ የሌላው ወገን ሐሳብና ስሜት ለመረዳት የማይችሉና ግልብ የሆኑ ከማስመሰሉም በላይ፤ ለግጭቱ መስፋፋትና መባባስም ምክኒያት ሊሆኑ ይችላሉ።

1. ጤነኝነት ያለው ግጭት የበለጠና የተሻለን ሐሳብ ለማግኘት፥ አዳዲስ የግል አስተሳሰቦች ለማስተዋልና ለማዳበር፥ ቤተ ክርስቲያኒቱን በተሻለ ሁኔታ ለማሳደግ ና አገልግሎታችንም እየሠመረ እንዲሄድ ለማድረግ እጅግ ጠቃሚ ነው።

2. ከእኛ ጋር የሚያገለግሉ አገልጋዮችም ይሁን፥ የምናገለግለው የእግዚአብሔ ር ሕዝብ ገንቢ ትችት፥ አለመስማማትና አለመረዳዳት በሚያመጡበት ጊዜ መገንዘ ብ ያለብን እነርሱም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጠራና በተሻለ ሁኔታ ለማሳደግ የሚፈልጉ መሆናቸውን ነው።

3. በጊዜው "የእኛ የግል ጠላቶች" አድርገን ከምናያቸው ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ለእኛ ለራሳችንም ሆነ፥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እጅግ ጠቃሚ የሆነ እውነት እንደ ሚኖራቸው በመቀበል፥ ልባችንንና መንፈሳችንን ክፍት ማድረግ አመራራችን እየደ መቀ እንዲሄድ ያደርገዋል።

4. በሕይወታችን ዘመን እጅግ የጠቀሙን የበለጠ በጥልቀትም ወደ ጌታ እንድ ንጠጋ ያደረጉን ሰዎች ጓደኞቻችን ወይንም የምንወዳቸው ቤተሰቦቻችን ሳይሆኑ፤ በትችት የወቀሱንና በከባድ ጡጫ የመቱንና ያቆሰሉን ሰዎች ናቸው። እነርሱ ናቸ ው የማይታየንን ነገር እንድናይ፥ ድካማችንን እንድንገነዘብና መሬት ረግጠን በሰከነ ሁኔታ እንድንጓዝ የረዱን። ስለዚህ እጅግ ጠቀሙን እንጂ፥ አልጎዱንም!!! እግዚአብ ሔርም እኛን ለማሳደግ የተጠቀመባቸው ሰዎች ናቸው!!!

**መ. አለመግባባትና ግጭት ሁሉ ባነካካን ጉዳይ ላይ ብቻ መወሰን አለበት፡-**

* ግጭትን ለመፍታት ከሌላው ሰው ጋር በምንወያይበት ጊዜ እኛ የቆምንበት አቋም በተለይም ያነሰና መረጃ የሌለው በሚሆንበት ጊዜ የተጋጨነው ሰው ውስጣዊ መንስኤ ልንጠይቅ እንጀምራለን፤ እርሱ ያደረገንን በመደጋገም ማጉረምረምና÷ ከምንነጋገርበት ጉዳይ ጋር የማይሄዱትን ነገሮችን አለ ቦታ ውና አለወቅቱ ማንሳት እንጀምራለን።

**ሠ.** እንደ እግዚአብሔር ሰዎች በግጭቱ ላይ መደማመጥ በሞላበት÷ የሁለት ወገን ምልልስ÷ ከተረዳንም በኋል የመጨረሻ መደምደሚያው ይቅርታ መጠያየቅና÷ "እኔ አጥፍቻለሁ፤ በድየሃለሁ!" የሚል መሆን ይኖርበታል። ይኼ አባባል ግን ከከን ፈር ያለፈ በእግዚአብሔር ፊት እያደረግነው እንዳለን በማስተዋልና መንፈስ ቅዱስ ም ለዚህ ምሥክር እንደሆነ በመገንዘብ ልናደርገው ይገባል። ይህንን ለማድረግ ፍጹም የሆነ ትሕትናና ብርታት÷ ቅንነትና የዋህነትን ይጠይቃል!!!

1. አንዳንድ ጊዜ የያዝነውን የራሳችንን ሐሳብ መልቀቅና÷ የሌላው ሰው ሐሳብ የተሻለ እንደሆነ መቀበል ሊሆን ይችላል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላው ሰው ትክክል እንደሆነና÷ እኛ ደግሞ የተሳሳትን መሆናችንን መዋጥ ሊሆን ይችላል።

2. ከዚህ ሁሉ ውይይት በኋላ እኛ ትክክል መሆናችንንና ሐሳባችን በላጭነት እንዳለው ብንገነዘብም÷ ሌላውን ሰው ከፍቅር የተነሣ ሊበልጥብንና የራሳችንን መብት እንኳን ሳይቀር በመስዋዕትነት መስጠት ልሆን ይችላል።

3. እዚህ ላይ ምንም ጊዜም መርሳት የሌለብን በሁለት መልካም ሰዎች መካከል ጣልቃ ገብቶ ግጭቱን የበለጠ ለማባባስና ለማቀጣጠል የሚፈልግ መንፈሳዊ ጠላታ ችን የሆነው ሰይጣን እንዳለም አንርሳ። ሐዋርያው ጳውሎስ፡- "*በሰይጣን እንዳንታለ ል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና።*" (2ቆሮ. 2÷ 11) እንዳለው ነው።
(የሐዋ. ሥራ 15÷ 36-41)

## VI. ግጭቶችን መፍታት በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ፡-

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከምናያቸው ግጥቶች መካከል የመጀመሪያይቱ የሐዋርያ ት ቤተ ክርስቲያን ያጋጠሟትን ሦስት ችግሮችን አንስተን በማየት፤ ሐዋርያት ለች ግሮቹ የነበራቸው መፍትሔ በመጠኑ ለመዳሰስ እንሞክራለን። ይኸን በምናደርግበት

ጊዜ ግን እንዲህ ዓይነት ችግሮች ቢነሱም "ምንም አይደለም" ለማለት አይደለም። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲህ ዓይነት መሳይ ችግሮች ቢነሱ ሐዋርያት ከነበራቸው የመፍትሔ ሐሳቦች በመነሳት መመርያዎቹን መውሰድ እንችላለን።

## ሀ. <u>*የግለሰቦች ግጭት*</u>፦ በሐዋርያው ጳውሎስና በበርናባስ መካከል (የሐዋርያት ሥራ 15፥ 36-41)

1. ከመጀመሪያው ጀምሮ የቡድን መንፈስና አብሮ ማገልገል የሚችልና የተሰጠ ልብ ነበረቸው።

2. ሁለቱም ስህተትና ጉድለት እንደሌለው ሰው እንደሆኑ አስበው አያውቁም።

3. በውይይታቸው ጊዜ አነጋጋሪው ጉዳይ ላይ እንጂ፥ ግለሰቡ ላይ በማነጣጠር ወይም በማተኮር አንዱ ሌላውን አንስተው አልተወያዩም። (የሐዋ. ሥራ 15፥ 37-38)

4. ሁለቱም በቅን ልብ ትክክል ነበሩ፦

✓ ማርቆስ አገልግሎቱን ጥሎ በመሄዱ ምክኒያት ጳውሎስ ልክ ነበር።

✓ እግዚአብሔር ተስፋ ባልቆረጠበት ሰው በማርቆስ ላይ ተስፋ ባለመቁረጥ በርናባስም ልክ ነበር።

5. በሁለቱ መካከል የተፈጠረው የግጭት መንፈስ ወደ ምዕመኑና ወደ አብያተ ክርስቲያናት አላሰራጩትም።

6. የግጭታቸው ውጤት "ላለመስማማት መስማማት" በመቻላቸው፦

- ጳውሎስ የሚያስገርም የአገልግሎት ቡድን አሳደገ። (ምሳሌ፦ ጢሞቴዎስ፥ ሲላስ፥ ቲቶ፥ አፍሮዲጡ፥ ሉቃስ፥ ወ.ዘ.ተ.)
- በርናባስ ማርቆስን በመያዙ፥ በመቅረፁና በማሳደጉ ምክኒያት እኛ ዛሬ የመጀመሪያ የሆነውን የማርቆስ ወንጌልን ለማግኘት ቻልን።
- ማርቆስም በእግዚአብሔር መንንግሥት ሥራ እጅግ የሚጠቅም ሰው ሆነ። (2ጢሞ. 4፥ 11)
- አብያተ ክርስቲያናትም እየፀኑና እየበረቱ ሄዱ። (የሐዋ. ሥራ 15፥ 41)
- የአውሮጳ አገሮችም ለመጀመሪያ ጊዜ በወንጌል ተደረሱ። (የሐዋ. ሥራ 16-20)

ለ. *የባሕል ግጭት*፡- (የሐዋ. ሥራ 6፥ 1-7)

1. የግጭቱ መነሻ የሆነው የቤተ ክርስቲያን እድገት ነበር፡፡ ከአሥራ ሁለት ---
--አንድ መቶ ሃያ -----ሦስት ሺ ------- አምስት ሺ ---------"ብዙ ሕዝብ!"
(ቁጥር 1)

2. አሥራ ሁለቱም ሐዋርያት በአንድነት መንፈስ ችግሩን ተጋፈጡ እንጂ፣
በየግላቸው ግጭቱን ሊፈቱ አልሞከሩም፡፡ (ቁጥር 2)

3. የእግዚአብሔር ቃል መመርያ እንዲመራቸውና እንዲገዛቸው አደረጉ እንጂ
፣ ለስሜታቸው ዕድል አልሰጡም፡፡ (ቁጥር 2-4)

4. የነበረውን አገልግሎት ሌሎችም እንዲሳተፉና እንዲወከሉ በማድረግ
መሥራት ጀመሩ እንጂ፣ አገልግሎቱ ሁሉ በእነርሱ እጅ ብቻ የተያዘ አላደረጉትም
(ቁጥር 2-4)

5. በሐዋርያት አስተሳሰብ በመሾምና በመምረጥ መሃል የተለጠጠና የደመቀ
ልዩነት አልነበረውም፡፡ (ቁጥር 3)

6. ግጭታቸውን በጥበብ የመፍታት ውጤት አስደናቂ ነው፡-

- "የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፡፡" (ቁጥር 7)
- "በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቁጥር እጅግ እየበዛ ሄደ፡፡" (ቁጥር 7)
- ከተመረጡትም መካከል እስጢፋኖስ ለጌታ ሥራ ለመነሣቱ፥ አንድ ኃይለኛ ስብከት መስበኩ፥ በዚህም ምክኒያት ስደት ለመነሣቱ፥ እና ወደየ አገሩም ለመበተናቸውና የጌታንም ራዕይና ጥሪ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ ዋና ምክኒያ ት ሆኗል!!!

ሐ. *የዶክትሪን ግጭት*፡- (የሐዋ. ሥራ 15፥ 1-35)

1. ሐዋርያትና ሽማግሌዎች በሙሉ የተሳተፉበት፥ ክፍትና፥ ግልፅ በሆነ ውይ
ይት ግጭት በፈጠረው ጉዳይ ላይ ተወያዩ፡፡ (ቁጥር 2፥ 7)

2. የግጭቱ መነሻ የሆነውን ችግር አስተዋሉ፡፡(ቁጥር 2፥ 5፤ ገላትያ 2፥ 3-14)

3. ትልቁን የሚያነጋግርና የሞትና የሕይወት ጉዳይ የሆነውን ችግር፤ ከትንሹ፥
ማለትም በመደረግ የሚጠፉና ቢደረጉ ባይደረጉ በቤተ ክርስቲያን ደህንነት ላይ
ለውጥ ከማያመጡት አነስተኛ ችግሮች ለዩ፡፡ (ቁጥር 19-29)

4. የሰዎችን የሕይወት ልምምድና የአገልግሎት ተሞክሮ ለመስማት እንዲችሉ ጊዜ ሰጡ። ልምሳሌ:- የጴጥሮስን (ቁጥር 7-11)፣ የጳውሎስንና የበርናባስን (ቁጥር 12)

5. ከሰዎች ልምምድ በላይ ሥልጣን ለሆነው ለእግዚአብሔር ቃል በቂ ጊዜ በመስጠት የውሳኔአቸው መመሪያና ጥበብ ለመስማት ልባቸውን ከፈቱ። (ቁጥር 13-21)

6. ሐዋርያት የወሰኑትን ውሳኔ ለአብያተ ክርስቲያናት በሁለት መንገዶች በኩል አስተላለፉ:-

- ጳውሎስና በርናባስ፥ ሌሎችም መሪዎች ተወካይ አድርገው ላኩ። (ቁጥር 22፥ 30-33)
- ውሳኔአቸውንም በደብዳቤ በጥንቃቄ ጽፈው ላኩ። (ቁጥር 23-30)

## VII. የግጭት ሰበብ :-

### ሀ. ግጭት የሚያመጣቸው ሰበቦች :-

- በሕይወት ላይ የማይመች፥ የሚጐረብጥና የሚያቆስል ነገር ያመጣል። ስለ ዚህም በመሠረቱ ደስ አይልም።
- ግጭት አንዳንዴ ልንለው፥ ወይንም ልናደርገው የማንፈልገውን ነገር እንድናደ ርግ ሊያስገድደን ይችላል። ስለዚህም እንጋለጣለን።
- አንድ ሰው ሲበድለን፥ ሳናስብ ልንናገር እንችላለን። ስለዚህም በኋላ የሚጸጽተን ቃላት ከአፋችን ስለምናወጣ መንፈሳችን ይቆሽሻል።
- የግጭቱ መነሻ ትንሽ ነገር ሆኖ፥ ልንወጣ ወደማንችልበት የክርክር ወጥመድ ውስጥ እንድንገባ ሊያደርገን ይችላል። ስለዚህም በነቃ መንፈስ ራሳችንን ልንቆ ጣጠር ይገባል።

### ለ. ግጭቱን ለመፍታት የምንጠቀምባቸው መንገዶች:-

1. ***<u>ከግጭቱ ለማምለጥ ምላሽ (ESCAPE RESPONSES)</u>:-***

ብዙዎቻችን ከግጭቱ ለመራቅና ለማምለጥ ስንል፥ ከተጋጨነው ሰው መራቅ፥ ችግሩ እንደሌለ መቁጠርና ስርጉዶ መያዝ፣ ወይንም አገልግሎቱን ጥሎ መሸሽ መፍ

ትሔ አድርገን እንወስዳለን:: እነዚህ መንገዶች ግን ግጭቱን ከሚፈቱ ይልቅ፣ የበለጠ እንዲከር ያደርጉታል::

1.1 መካድ ወይም መሰርጎድ፥ እንደሌለ መቁጠር (DENIAL)፥

አንዱ ከችግሩ ለማምለጥ ስንፈልግ የምንጠቀምበት መንገድ ችግሩ እንደሌለ፥ ሰጎን ችግሩን እያየች እንዳላየች እንደምትሆን ዓይነት ነው:: ይኼ ለጊዜው እፎይታን ያመጣ ይምሰል እንጂ፣ እየዋለና እያደረ ግን ችግሩ እንዲባባስ ያደርገዋል:: (1ሳሙ. 2፥ 22-25፥ 29-30)

1.2 ከነገሩ መሸሽ ወይም መራቅ (FLIGHT)፦

ሌላው ከችግሩ ለማምለጥ የምንጠቀምበት መንገድ ከነገሩ መሸሽ፥ መራቅ፥ ከተጣላናቸው ሰዎች እየራቅን መሄድ ሊሆን ይችላል:: ይኸ ማለት ጓደኝነትን ማቋረጥ፥ አገልግሎትን ማቆም፥ ሥራን መተው፥ ትዳርን ለማፍረስ ለፍቺ ፍርድ ቤት ፋይል ማስገባት፥ ወይንም ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን መቀየርና፥ ወ.ዘ.ተ. ሊሆን ይችላል::

❖ <u>ብዙ ሰዎች አብዛኛው ዘመናቸውን ያሳለፉት በጣም ከሚወዷቸውና ከሚያከብሯቸው ሰዎች ጋር ሳይሆን፣ ከሚጠሏቸው ሰዎች ጋር ነው!!! ሲበሉ፥ ሲተኙ፥ በሀልማቸው፥ ሲፀልዩ፥ በሞቀ አምልኮ ላይ እያሉ፥ ሲያገለግሉ፥ ወደ ሐሳባቸው እየመጡ ጣልቃ ይገቡባቸውና መንፈሳቸው እንዲታወክ ያደርጋል::</u>

1.3 በራስ ላይ ጉዳት ማምጣት፦

ሰዎች ችግራቸውንና ያጋጠማቸውን ግጭት ለመፍታት አቅም ሲያንሳቸው በራሳቸው ላይ ጉዳትን ሊያመጡ ይችላሉ:: እዚህ ላይ ከመድረሳቸው በፊት ግን የሚረዳቸው፥ የሚመክራቸው፥ የሚሰማቸውና የሚጸልይላቸው ሁነኛ የእግዚአብሔር ሰው ያስፈልጋቸዋል::

## <u>*2. የማጥቃት ምላሽ (ATTACK RESPONSES) ፦*</u>

ሌሎች ሰዎች ደግሞ አጠፌታውን ለመመለስ የማጥቃት እርምጃዎችና መንገዶችን በመጠቀም ሁልጊዜ "እነርሱ ልክ" እንደሆኑ ለመግለፅ ጡንቻቸውን ያጠፍራሉ:: (TO FIGHT!)

2.1 የስም ማጥፋት ዘመቻ (ASSAULT) :-

አንዳንድ ሰዎች ግጭቱን ከመፍታት ይልቅ፤ ፍጥጫ መፍጠር፥ የቃላት ድንጋይ መወርወር፥ ሐሜታና የአሽሙር ንግግር ማሠራጨት፥ ሥጋዊ አመፅ (መማታት) ማካሄድ፥ በደለን የሚሉትን ሰው በገንዘብ፥ ወይም በፕሮፌሽን ማጥቃትን ይወዳሉ:: (የሐዋ. ሥራ 6፥ 8-15) እንዲህ ዓይነት አካሄድ ግን ችግሩን የበለጠ እየተሳከረ እንዲመጣ ያደርገዋል::

2.2 በሕግ መክሰስ (LITIGATION) :-

አንዳንድ ጉዳዮች ምንም እንኳን በፍትሀ ብሔር (CIVIL COURT) ዳኛ ፊት በመቅረብ ሊፈታ ቢችልም (የሐዋ. ሥራ 24፥ 1-26፤ ሮሜ 13፥ 1-5)፤ የነበረውን የግንኙነት ሥምረት ከማበላሸቱም በላይ፥ የክርስቲያን ምሥክርነታችንን ያበላሻል:: አብዛኛውን ጊዜ ትክክለኛና ፍፁም ፍትሕ ሳያገኝ ይቀራል:: ስለዚህም ነው ክርስቲያኖች በመሃላቸው ያለውን ችግር ወደ ፍርድ ቤት ከመውሰድ ይልቅ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማምጣትና መፍትሔ ማግኘት ያለባቸው:: (1ቆሮ. 6፥ 1-8፤ ማቴ. 5፥ 25-26፥ 18፥ 15-20)

2.3 የሥጋ ግድያ (MURDER) :-

በጣም የከረረ፥ ቅጥ ያጣና፥ መንፈሳዊነት የጎደለው ሰው በሚሆንበት ጊዜ የበደለውን ሰው ሕይወት በማጥፋት፥ በመግደልና ወንጀል በመፈፀም መፍትሔ የሚያገኝ ይመስለዋል:: (የሐዋ. ሥራ 7፥ 54-58) <u>ክርስቲያኖች ከሆንን ምንም ቢሆን የሥጋ ግድያ ሙከራ በማንም ሰው ላይ ባናደርግም፤ በጥላቻ፥ መራራ በሆነ መንፈስ፥ በቂምና በበቀል ስሜት በመጠመድ ወንድማችንን ወይም እህታችንን ለመግደል እንደምንችልና፤ በእግዚአብሔርም ፊት የሚያስጠይቀን እንደ ሆነ ልንገነዘብ ይገባል::</u> (ማቴ. 5፥ 21-26፤ 1ዮሐ. 3፥ 15)

**ሐ. ሰላምና እርቅን የማምጣት ምላሾች:-**

***<u>1. በግል ሰላምን ማምጣት :- (PERSONAL PEACEMAKING)</u>:-***

በግል ሰላምን ለማምጣት የሚረዱን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መንገዶች ግጭቱን ለመፍታትና ከሌላው ወገን ጋር ተነጋግሮ መፍትሔና እልባት ለማግኘት የምንጠቀምባቸው መንገዶች አሉ::

1.1 ችግሩን በልበ ሰፊነት አይቶ መተው :-

አብዛኛዎቹ የሚያከራክሩን ነገሮች ቁም ነገር የሌላቸውና አነስተኛ ጉዳዮች ከመሆናቸውም በላይ÷ ከጊዜ በኋላ ለምን እንደተፈጠሩ የሚያሳፍሩን ጉዳዮች ናቸው:: በመጽሐፈ ምሳሌ 19÷11 ላይ "ሰውን ጠቢብ አዕምሮው ከቁጣ ያዘገየዋል÷ ለበደለኛውም ይቅር ይል ዘንድ ክብር ይሆንለታል::" ይላል:: ችግሩን በልበ ሰፊነት አይቶ ለመተው መቻል ይቅርታ ማድረግም ነው:: ምንም ዓይነት ንግግር ሳያስፈልገው÷ በጉዳዩም መቆየት ሳያስፈልግ÷ መራራ ለሆነ መንፈስና ለቁጣም ራሳችንን ላናስገዛ መተው መቻል መታደልና በረከት ነው!!!

1.2 እርቅን ማካሄድ:-

የተፈጠረው ችግር የጠለቀና ብዙ ነገር የሚያስከትልና የሚያበላሽ መሆኑን ካስተዋልን÷ ግንኙነታችን እየሻከረ ከሚመጣና የእግዚአብሔርንም ሥራ ከሚጎዳ ይልቅ፣ መደማመጥ በሞላበት ሁኔታ÷ በእርጋታ÷ ንስሀ ገብቶና ይቅርታ ተጠያይቆ በምህረት በመቀባበል የእርቅ መንፈስ እንዲመጣ ማድረግ የጠለቀ መንፈሳዊነት ነው:: (ማቴ. 5÷23-24፤ ገላ. 6÷1፤ ማቴ. 18÷15-20፤ ኤፌ. 4÷32)

1.3 ከእርቅ በኋላ መስማማት (NEGOTIATION):-

ምንም እንኳን በግላችን ብንታረቅም÷ ምን አልባት በገንዘብ÷ በንብረት÷ ወይም በሃብት ጉዳይ ላይ ግን መስማማት ተወያይተን ዘላቂነት ያለው መፍትሔ ማምጣት ያስፈልግ ይሆናል:: (ፊል. 2÷4)

## <u>2. አስታራቂ ሰዎች እየረዱን ሰላምን÷ ይቅርታንና እርቅን ማምጣት</u>

## <u>*(ASSISTED PEACEMAKING)*</u> :-

በግላችን ችግሮችን መፍታት ካልቻልን÷ ሊረዱንና በመሃላችንም ሆነው ሊመክሩን የሚችሉ ሰዎችን ማስገባቱ ጥበብ ነው::

2.1 ማስታረቅ (MEDIATION) :-

ሁለት ሰዎች በግላቸው ለመስማማት ካልቻሉ÷ ነገሩን በጥሞና አድምጠው በጥበብ ሊይዙና የእነርሱንም መታረቅ የሚወዱ÷ ሚስጥራቸውንም ሊጠብቁ የሚችሉ የእግዚአብሔር ሰዎች በመሃላቸው ገብተው እንዲያስታርቋቸው መጠየቅ በጣም አስፈላጊ ነው:: (ማቴ. 18÷16) እነዚህ በመሃል ገብተው የሚያስታርቁ ሰዎች የፈለጉትን ጥያቄ ሊጠይቁ÷ ሊመክሩና ሊገስፁ እንዲችሉ ሙሉ ነፃነት ሊሰጣቸው ይገባል ብዬ አምናለሁ::

2.2 ማደራደር (ARBITRATION) :-

ሁለት የተጣሉ ሰዎች በፈቃዳቸው ለመስማማት ካልቻሉ፥ በተለይም የገንዘብ፥ ንብረት፥ ወይም ሀብት ጉዳይ ላይ ብያኔ እንዲሰጡና እልባት የሚያመጣ የውሳኔ ብይን የሚወስኑ አደራዳሪ ሰዎች መጋበዝ አለባቸው::(1ቆሮ. 6፥4)

2.3 ተጠያቂነትና ዲሲፕልን (DISCIPLINE) :-

አንድ ሰው ክርስቲያን ሆኖ ለመታረቅ ባይፈልግና እውነትን ለመቀበል ባይችል ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያንን ሰው በኃላፊነት ተጠያቂ እንዲሆን ሊያደርጉና፤ ከዚያም አልፈው ወደ ንስሀ፥ ፍትህና፥ ይቅርታ ለማምጣት እንዲችል ዲሲፕልን ሊያደርጉት ይገባል:: (ማቴ. 18፥17፤ 1ቆሮ. 6፥3፥5)

### መ. በትክክል ያልተያዘ ግጭት :-

1. በመካድ ሲያዝና ለመፍታት ሳይፈለግ ሲቀር :-

1.1 ቁጣን አለቦታውና ለማይገባው ሰው መግለፅ እንጀምራለን::

1.2 ወይንም የዚህ ተቃራኒ ከቁጣ ራሳችንን ማግለል፥ ለዘብተኛ መሆንና፥ ግድ የለሽነትን እንለማመዳለን::

1.3 ቁጣውን ማናናቅ፥ አሳንሶ ማየት::

2. ችግሮችን ለመፍታት አለመቻል:-

2.1 ትችት ማብዛት፥ የአሽሙር ንግግር መናገር፥ በአእምሮ ጡንቻ መማታት::

2.2 ስለ ራስ መሟገት፥ ራስን ከሚገባ በላይ መከላከል::

2.3 ዓይን ያወጣ በቀል ለመወጣት የተለያዩ የጥላቻ መንገዶችን መጠቀም::

2.4 አኩርፎ መሰንበት፥ ጉንጭ ማሳበጥ፥ ችግሩን በሌላው ሰው ላይ መለደፍ፥ ቁጣን ውጦ መቀመጥ::

## VIII. ግጭትን ለመፍታት መታሰብ ያለባቸው ጉዳዮች :-

### ሀ. የግጭቱን ዓይነት ማወቅና መወሰን :-

1. ዋናው የግጭቱን ዓይነት መለየት፥ ትልቅ ጉዳይ ወይም ትንሽና በመደረግ የሚጠፋ ነገር መሆኑን መለየት፥ ለችግሩ መነሳት የሆኑትን ምክኒያቶች ማወቅ፥ በዚህም ውስጥ ለችግሩ ያደረግነው አስተዋፅዖ ምን እንደሆነ መገንዘብ፥ በምን መንገድ ሊፈታ እንደሚችል በጥንቃቄ ከብዙ ጸሎት ጋር ፕላን ማውጣት::

2. የችግሮቹ ዓይነት በርካታ ከሆነ የትኛው ከየትኛው መቅደም እንዳለበት መወሰን÷ ቅደም ተከተል ማውጣት÷ ቶሎ መደረግ ያለበትና መቆየት የሚችለውን ለይቶ ማወቅ::

**ለ. ችግሩን ለመፍታት ትክክለኛውን ጊዜ መምረጥ :-**

1. የስሜት መናር የሌለበትና በእርጋታ መናገር የሚቻልበትን ወቅት መምረጥ ÷ ከእጅ ሳይወጣ በወቅቱ መፍታት::

2. ለእኛም ሆነ ለምናነጋግረው ሰው የሚመች ጊዜና ወቅት መወሰን:: አለበለዚያ አላስፈላጊ የሆነ ውጥረት ሊፈጥር ይችላል::

**ሐ. ችግሩን ለመወያየት የሚያስችል ትክክለኛውን ቦታ መምረጥ:-**

1. ለሁለታችን የሚስማማ ቦታ መሆኑን ማረጋገጥ::

2. ሌሎች ሰዎች ሊሰሙ በማይችሉበትና ጣልቃ የሚገባ ነገር በሌለበት ÷ ጸጥታና እርጋታ ያለበት ሥፍራ መምረጥ::

**መ. በመልካምና ከሌላው ሰው ጋር የምናየው በጎ የሆኑ ባህርያትን በመጥቀስ መጀመር:-**

1. የንግግራችን አወጣጥ ሳይቀር ጸጋ የተሞላና የተረጋጋ መንፈስ በሞላው ልብ ሐሳባችንን መግለፅ::

2. ሌላው ሰው ለሕይወታችን ያደረገውን አስተዋፀዖና ከእርሱም የተማርናቸው ን ነገሮች ማካፈልና ማመስገን::

3. የመነጋገራችን መነሻና መሠረት ለእርሱም ካለን ፍቅርና አክብሮት የተነሳ እንደሆነ ማሳየት::

**ሠ. የችግሩ መነሻ በሆነው ጉዳይ ላይ ማተኮር:-**

1. በተለይም ሌላው ሰው የተያያዘ ሌላ ነገር ለማምጣት በሚፈልግበት ጊዜ የነገሩ ቅርንጫፍ እየበዛ እንዳይሄድ በዋና ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር መርዳትና÷ መልሶ ወደዚያው ሐሳብ ማምጣት::

2. በመደረግ የሚጠፉና እግረ መንገድ በተነሡ ጉዳዮች ላይ ከመነጋገር መቆጠብ::

ረ. ከዚህ በፊት የፈታነውን ችግር አዳምሮ አለማምጣት:-

1. ባለፈው ጊዜ የተጎዳዳነው ነገር ካለ አሁን ካለው ችግር ጋር አዳምረን ለማምጣት መፈተናችን ስለማይቀር÷ ራሳችንን መግታትና መልሰን በመደጋገም አለመነጋገር::

2. ሌላው ሰው ያጠራቀመውን ቁጣ በእኛ ላይ ለመወጣት ስለሚፈልግ በትዕግስትና በጥበብ ለማርገብ መቻል::

ሰ. የሚያሳምምና አጥንትን የሚሰብር ነገር ከመናገር መቆጠብ:-

1. የአዕምሮ ጡንቻን በመጠቀም በቃላት ዱላ ሌላውን ሰው ከመጉዳት መታገድ::

2. የሌላውን ሰው ስሜት የሚጎዱ የሕይወት ጓዳዎችን በመፈለግ በጭካኔ ለመውጋት አለመሞከር::

ሽ. ሌላውን ሰው በአክብሮት መቀበልና በቁም ነገር መውሰድ:-

1. ማንቋሸሽም ይሁን÷ ወይም በእርሱ ላይ መሳቅ የክርስቲያን ባሕርይ አይደለም::

2. እንዲህ ዓይነት አቀራረብ "አትረባም÷ አትችልም÷ አታውቅም÷ ወይንም አትጠቅምም" የሚሉ ያልተፈለጉ መልዕክቶችን ስለሚያስተላልፍ ሰውዬውን እጅግ ይጐዳዋል::

3. እርሱም በተራው አጠፌታውን እንዲመልስ ያስገድደዋል::

ቀ. ምናልባት መቆጣት ካስፈለገ ሌላውን በሚጎዳ መልክ እንዳይሆን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግና÷ በዕድቅ የተለወሰ ቁጣ መሆኑን ማረጋገጥ:: (ኤፌ. 4÷ 26)

በ. የምንነጋገረው የከበረ ስብዕና ካለው ሰው ጋር ስለሆነ ጨዋታ እንደሚጫወት ሰው አናድርገው::

ተ. በድብቅና ምሥጢራዊ በሆነ መንገድ ሌላውን ሰው የሚያጠቃ ከመሆን ራሳችንን መግዛት::

ቸ. ሌላው ሰው ላደረገው ነገር ምክኒያታዊ ነገሮችን እንዲሰጥ መጠየቅ ችግሩን የበለጠ ያሳክረዋል::

ኀ. ሌላውን ሰው በተለያየ ስያሜ መጥራትም ይሁን÷ ድፍን አድርጎ የችግሩ ምክኒያት እንደሆነ መናገር ምንም ዓይነት የሚገነባ ውይይት ለማካሄድ እንዳይችል ያደርገዋል::

ነ. ከምንነጋገረው ሰው ሌላ ሦስተኛ ሰው እንዲደረብ ማድረግና (ለምሳሌ:- ልጆቻችንን በመሃላችን ማምጣት)÷ የራሳችንን ሐሳብ ድጋፍ ለማግኘት መሞከር ችግሩ የበለጠ የተወሳሰበ ያደርገዋል::

## IX. ግጭቶችን የመፍታት ዓይነቶች ወይም ደረጃዎች:-

### ሀ. ሌላውን ሰው ማራቅ (AVOIDANCE) :-

በከፍተኛ ደረጃ በነገሩ ለመተባበርም ይሁን እርግጠኛ ከመሆን ቁጥቦች የሆኑ ሰዎች የሚያሳዩት ባህርይ ነው:: (ማቴ. 12÷ 9-21፤ ሉቃስ 22÷ 39-41)

### ለ. ሌላውን ሰው መቅረብ (ACCOMODATION):-

በነገሩ ለመተባበር ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው÷ ሆኖም ግን እርግጠኝነት የሌላቸው ልዝብና የማይጓጉ ሰዎች የሚያሳዩት ባሕርይ ነው:: (ማቴ. 26÷ 50-53)

### ሐ. ከሌላው ሰው ጋር መፎካከር (COMPETITION):-

በጣም ዝቅተኛ የሆነ የመተባበር ፍላጎት ያላቸውና እርገጣኝነታቸው ግን ከፍተኛ የሆኑ ሁልጊዜ ለማሸነፍ የሚፈልጉ ሰዎች ባሕርይ ነው::

### መ. ከሌላው ሰው ጋር ማመቻመች (COMPROMISE):-

በመጠኑም ቢሆን ለመተባበር ፍላጎት ያላቸውና እርግጠኝነታቸውም ያልከረረ ባሕርይ ያላቸው ሰዎች የሚገልፁት ነው::

### ሠ. ከሌላው ሰው ጋር መተባበር (COLLABORATION):-

ከፍተኛ የሆነ መተባበርና እርገጠኝነት ማሳየት የሚችሉና÷ ችግርንም ለመፍታት ሙሉ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩት ባሕርይ ነው::